*Ethiop.j.lang.cult.commun. 2025, 10*(2): 173-184
*Faculty of Humanities-Bahir Dar University*
*ISSN: 2518-2919*
DOI 10.20372/ejlcc.v10i2.2962
*Open Access Licensed under Creative Commons: CC BY-NC-ND 4.0*

**Original Research** **Open Access**

# An analysis of the perception of purification from impurity through the GIs ritual in the Basoliben community

**Muluken Yenesew Tiruneh***
PhD candidate, Bahir Dar University, Ethiopia

**Waltenigus Mekonnen (PhD)**
Assisstent Professor, Bahir Dar University, Ethiopia

**Lemma Nigatu (PhD)**
Associate Professor, Jimma University, Ethiopia

**Corresponding Author: mulukenyenesew@gmail.com*

Abstract

This study investigates how the Basoliben community perceives the ritual of "Gis" as a means of purfyng impurity. The main reason for this study is that there is a gap in studies focusing on the concepts of impurity and purification in Ethiopia, both in cultural studies and other academic disciplines. In the study, from the twenty-five kebeles found in Basoliben woreda, five kebeles were selected by purposive and snowball sampling techniques. The primary data were collected through observation, interviews, and focused group discussions in natural setting. The gathered data were analyzed using a descriptive and content analysis method, framed by structural-functionalism and purification-defilment or impurity theory approaches. The finding of the study indicat that, for the Basoliben community, one of the mechanisms used to purify what is considered defilement is the 'Gis' ritual which serves as an institutionalized way of preserving social values. The study reveals that the Gis ritual is performed by sprinkling blood and its goal is to protect the health of people and animals, as well as to cleanse diseases related to epidemics and curses. Furthermore, the Gis ritual is not performed by individually, but through criteria that can bring people together. It is seen as a method of keeping purity in the community by avoiding defile behaviors that could jeopardize their social cohesiveness. Overall, the findings show that the community's observance of the Gis ritual serves as a means of maintaining cleanliness by avoiding undesirable acts that may harm unity, cause loss of production, or affect health. Likewise, adhering to the rules applied the norms of Gis ritual is a symbol of purity, and the diseases that results from not observing the norms and values is considered defilement.

Key words: Purification, Impurity, Gis, Basoliben, Ritual, social ties & norms, cultural values

*Ethiop.j.lang.cult.commun. 2025, 10*(2): 173-184
*Faculty of Humanities-Bahir Dar University*
*ISSN: 2518-2919*
DOI 10.20372/ejlcc.v10i2.2962
*Open Access Licensed under Creative Commons: CC BY-NC-ND 4.0*

## በግስ ሥርዓት ርኩሰትን የማንጻት እሳቤ ትንተና በባሶሊበን ማኅበረሰብ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ‹‹በባሶሊበን ማኅበረሰብ በግስ ሥርዓት ርኩሰትን የማንጻት እሳቤ›› ምን እንደሚመስል መመርመር ነው፡፡ የጥናቱ መነሻ ምክንያት በኢትዮጵያ ውስጥ በባህል ጥናትም ሆነ በሌሎች የትምህርት ዘርፎች፣ የርኩሰትና የመንጻት እሳቤን ማዕከል ያደረጉ ጥናቶች ክፍተት መኖሩ ነው፡፡ በጥናቱ በባሶሊበን ወረዳ ከሚገኙ ሃያ አምስት ቀበሌዎች መካከል አምስት ቀበሌዎችን በዓላማ ተኮርና ቅብብሎሽ ናሙና ስልት በመምረጥ በተፈጥሯዊ መቼት በመጠቀም መረጃው በምልከታ እንዲሁም በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ተሰብስቧል፡፡ የተሰበሰበው መረጃ በመዋቅራዊ-ተግባራዊነት እና የመንጻትና መርከስ ቲዎሪ /purification-defilment/impurity theory በመታቀፍ በገለጻና ይዘት ትንተና ስልት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ የጥናቱ ውጤት የሚያሳየው የባሶሊበን ማኅበረሰብ ርኩሰት የሚላቸውን ነገሮች ከሚያነጻባቸው መንገዶች አንዱ፤ ግስ ሥርዓትን በመተግበር ማኅበራዊ እሴትን ማስጠበቂያ መሆኑን ነው፡፡ የግስ ሥርዓት የሚከወነው ለሥርዓቱ ተቀባይነት ያለው የበግ ደም በመርጨት እንደሆነና ግቡም፤ የሰዎችንና የእንስሳቱን ጤንነት ለመጠበቅና የወረርሽኝና የመቅሰፍት በሽታዎችን ለማንጻት መሆኑን መረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡ በተጨማሪም የግስ ሥርዓቱ የሚከወነው በተናጠል ሳይሆን ሰዎችን ሊያሰባስቡ በሚያስችሉ መስፈርቶች በመጠቀም ሲሆን፣ ማኅበራዊ አንድነታቸውን ከሚያረክስ አላስፈላጊ ድርጊት ሁሉ መጠበቅ ንጽሕናን በአካባቢው ላይ እንደማስፈን ይቆጠራል፡፡ በአጠቃላይ በጥናቱ ውጤት ማኅበረሰቡ የግስ ሥርዓትን ሲከውን፤ አብሮነትን ከሚያፈርስ፣ ሃብትን ከሚያሳጣ እና ጤንነትን ከሚጎዳ አላስፈላጊ ነገር በመጠበቅ ለንጽሕና መጠበቂያ ሥርዓቱ ተገዢ የሚሆንባቸውን መንገዶች አሳይቷል፡፡ እንዲሁም በግስ ሥርዓቱ የሚተገበሩ ደንቦችን መጠበቅ የንጽህና መገለጫ ሲሆን፣ ደንቡን ባለመጠበቅ የሚከሰተው ህመምና ችግር ደግሞ ርኩሰት ስለመሆኑ የጥናቱ ግኝት አረጋግጧል፡፡

**Citation:** Muluken Yenesew Tiruneh, Waltenigus Mekonnen & Lemma Nigatu. (2025). An analysis of the perception of purification from impurity through the GIs ritual in the Basoliben community. *EJLCC, 10*(2).173-184. DOI 10.20372/ejlcc.v10i2.2962

| *Submitted: April 2025* | *Revised: August 2025* | *Accepted: September 2025* |

**©2025 Author(s). All rights reserved**

# የጥናቱ ዳራ

ሰዎች በዓለም ላይ ሲኖሩ በባህላዊ እሴቶቻቸው ውስጥ የሚተገብሯቸው የተለያዩ ሥርዓቶች አሏቸው፡፡ Jordan (2021)[1]፣ ‹‹ማኅበራዊ እሴቶች በሰዎች የተለያዩ መስተጋብሮች የተፈጠሩ እና ለሰው ልጆች አብሮነትና ደህንነት መሠረት ናቸው›› ይላሉ፡፡ ስለሆነም፣ በማኅበራዊ እሴቶች ውስጥ ሰዎች የሚመሩባቸው የተለያዩ ማኅበራዊ ደንቦች ይኖራቸዋል፤ በማኅበራዊ እሴቶችና ደንቦች ህግ ውስጥ ደግሞ የርኩሰትና ንጽሕና ጽንስ ሃሳብ ይገኝበታል፡፡ ምክንያቱም፣ በቡድኖች ውስጥ የርኩሰት ተግባራት ከተከሰቱ የእሴት ደንብ ጥሰት መኖሩ አይቀሬ ነው፡፡ ስለሆነም፣ የመንጻት እና የመርከስ ጽንስ-ሐሳቦች ተቃራኒ ቢሆኑም እርስ በርስ የተቆራኙ ናቸው፤ የአንዱ መኖር ለሌላኛው ህልውና መሰረት ይሰጣል። ይህንንም በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን ማብራሪያ ይሰጣሉ።

Fardon (2016) እና Feder (2021) ርኩሰት በሃይማኖታዊም ሆነ በባህላዊ አውዶች በአካል የቆሸሹ ነገሮች ወይም ሰዎችን ለመግለጽ የሚያገለግል ቃል መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ Blidstein (2017) በበኩላቸው፣ ርኩሰት ከዚህ አልፎ የስነልቡናዊ አፀያፊ ስሜትንና የብክለት ስሜትን (emotions of disgust and contamination) እንዲሁም የሰዎችን አጠቃላይ ሞራላዊ ደረጃ ለማመልከት ጥቅም ላይ እንደሚውል ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም፣ መርከስ[2] ማለት አንድ ማኅበረሰብ በእምነቱ ወይም በባህሉ በማይፈቅዳቸው ሁነቶች (ተፈጥሯዊም ቢሆኑ) በመሳተፍ የሚመጣ መቆሸሽ መሆኑን ያብራራሉ። በሌላ በኩል Feder (2016) ርኩሰትን "ንጹሕ ባልሆኑ ወይም አደገኛ በሆኑ ነገሮች ንክኪ አማካኝነት ይመጣል ተብሎ የሚታመንበት የህመም ዓይነት" እንደሆነ ገልጸዋል። ሃሳቦቹ እንደሚያሳዩት ርኩሰት ከሥርዓት ጥሰት ባሻገር ጤንነትን ለሚጎዱ በሽታዎች ማሳያ ስለመሆናቸው ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም Lockett (2008) ደግሞ ርኩሰት፣ /impurity ኃጢያት /sin ከመስራት ጋር እንደሚያያዝ ይጠቁማሉ፡፡ በLockett

[1] በዚህ ጥናት የተጠቀሱት ምንጮች ስማቸውን ተከትሎ በእንግሊዝኛ የተጠቀሱት ኢ.ኤ.አ ሲሆን፣ በአማርኛ የተጻፉት ደግሞ በኢ.ትዮጵያን አቆጣጠር በዓ.ም ቀርበዋል፡፡

[2] መርከስን የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (2014) ነውረኛ፣ አስጸያፊ መሆን፣ ግንኙነትን የሚያፈርስ በማለት ይገልጸዋል፡፡ የኢ.ትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር መዝገበ ቃላት(1993) ይህንን ሃሳብ ከመጋራት ባሻገር ቅን የማያስብ፣ ክፉ የተጠላ፣ ቅዱስ ያልሆነ ይለዋል፡፡

ገለጻ፣ “ኃጢያት” የባህርይ መርከስን የሚያሳይ በመሆኑ “ርኩሰት”ን የሚገልጽ ቢሆንም ኃጢያት ርኩሰት የሚለውን እሳቤ ሊተካው እንደማይችል ያብራራሉ፡፡ በመሆኑም የርኩሰት ጽንስ ሐሳብ በኃጢያት ከመርከስ ብያኔው ባሻገር በሌሎች ማኅበረ-ባህላዊ መዋቅሮች ውስጥ የማንነት ማሳያና መግለጫ በሆኑ እሴቶችም የሚበየን ስለመሆኑ ሌሎች ምሁራን ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ አንጻር Das (2008) እና Reimer (2006) መርከስ ተፈላጊ ያልሆነን ነገር መከተል፤ ትዕዛዝን ወይም ደንብን መጣስ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ይኸ ሃሳብ ርኩሰት ከተለመደው ህግ ከመውጣት ጋር የተያያዘ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

Douglas (2003) ደግሞ መርከስ፣ ከሥርዓታዊነት ወደ ሥ ርዓት ማጣት፣ ከመሆን ወደ አለመሆን፣ ቅርጽ ይዞ ከነበረው ወደ ቅርጽ አልባነት፣ ከሕይወት ወደ ሞት የሚወስዱ ጉዞዎች የሚንጸባረቁበት መሆኑንና ትንታኔያቸው እንደዚህ ባሉ ጥልቅ ጭብጦች ላይ የሚያተኩር ስለመሆኑ አብራርተዋል፡፡ በመሆኑም፣ ከላይ የቀረቡት ጽሑፎች የሚያሳዩት የርኩሰት ብያኔ ከኃይማኖታዊው አውድ ባሻገር በማኅበረ-ባህላዊ ስርዓት ውስጥ ያሉ የእሴት ደንቦችን በመጣስ ከሚፈጸሙ የህግ መተላለፎች ጋር የተያያዙ እሳቤዎች የሚጠኑበት መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ በዚህ ጥናት በግስ ማኅበረ-ባህላዊ ሥርዓት ውስጥ የሚተገበሩ ክዋኔዎች ከማኅበራዊ ግንኙነቶች እና ከባህላዊ ደንቦች መተላለፍ ጋር የተያያዙ ተግባራት ማሳያ የሆኑ ጉዳዮች ይብራሩበታል፡፡

ከላይ የቀረቡት የርኩሰት ብያኔዎች የመንጻት ጽንስ ሐሳብ ርኩሰትን ለመግታት የሚፈጸም ሥርዓት መሆኑን ያሳያሉ፡፡ Douglas (2003) መንጻት በኃይማኖታዊ አውድ በኃጢያት መርከስን ለማስወገድ ሲባል ትኩረት የሚደረግበት ተግባር መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በሌላ በኩል McKinney (2022) ‹‹መንጻት በቡድን ወይም በግል የሚከሰት ርኩሰትን ለማንጻት የሚተገበሩ ምግባራዊ ወይም ሃይማኖታዊ እሳቤዎች ሊሆኑ ይችላሉ፤ የማንጻት ሥርዓቱም ከበራዊ ወይም በሌላ መንገድ ሊሆን ይችላል›› ይላሉ፡፡ ከዚህ ሃሳብ ጋር በተያያዘ Blidstein (2017) እና Bell (2009) የመንጻት[3] ሥርዓቶች በተለያዩ መንገዶች እንደሚከናወኑ ይገልጻሉ። እንደ እርሳቸው ገለጻ፣

---

[3] Feder (2021፡13) ንጽህና/መንጻት የሚለውን ቃል የአሜሪካን የቅርስ መዝገብ ዲክሽነሪ ተመሳሳይ የሆነ ስሪት/ያልተቀላቀለ፤ ያልረከሰ፤ ያልተበከለ፤ የተሟላ፤ ትክክለኛ፤ ድንግል/አዲስ የሚሉትን ብያኔዎች ያቀረበበት ሲሆን ትርጉሞቹ በርክሰት ተቃራኒነት የሚፈረጁ ቃላት ናቸው፡፡

እነዚህ ሥርዓቶች ሰዎችን ከኢጋንንት፣ ከኃጢአት፣ ከበሽታ እና ካለፉ አላስፈላጊ የህይወት ልምዶች ነፃ ለማውጣት ያለሙ ናቸው። አንዳንዶቹ ሥርዓቶች በግለሰብ ደረጃ በሚፈጸሙ ጥፋቶች ላይ ትኩረት ሲያደርጉ፣ ሌሎች ደግሞ ማኅበረሰብን በአጠቃላይ ከሚጎዱ ተላላፊ በሽታዎች ለመከላከል ያለሙ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

ይህ ሃሳብ፣ የመንጻት ሥርዓቶች ማኅበረሰብን ከሚያውኩ ክስተቶች በመጠበቅ ጤናማ ማኅበረሰብን ለመገንባት ያላቸውን ጉልህ ሚና ያሳያል። Akter (2023) እና Duschinsky et al. (2016) መንጻትና መርከስ በተፈጥሮ የተገኙ ሳይሆኑ በማኅበረ-ባህላዊ እውቀቶች የተገነቡ በመሆናቸው ይስማማሉ፡፡ ስለሆነም፣ ንጽሕና እና ርኩሰት በማኅበረሰቡ በተገነባ የወል እሴት ሥርዓት ውስጥ የሚኖሩ ግንዛቤዎች በመሆናቸው ርኩሰት መከሰቱን የሚወስነው የባህሉ ባለቤት ንጽሕናን በተገነዘበበት መንገድ ነው፡፡

ይኽ ጥናት ትኩረት ያደረገበት የባሶ ሊበን ወረዳ፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ በምስራቅ ጎጃም አስተዳደራዊ ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ወረዳው፣ የምስራቅ ጎጃም ዞን ዋና ከተማ ከሆነችው ደብረ ማርቆስ፣ በስተ ደቡብ 27 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ ወረዳዋን በምስራቅ አዋባልና አነዳድ ወረዳ በምዕራብና ሰሜን ጎዛምን ወረዳ በደቡብ ምስራቅና በደቡብ ምዕራብ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ያዋስኗታል፡፡ የወረዳዋ ዋና ከተማ የጁቤ የምትባል ሲሆን፣ ኮርክ እና የላምገንጅ የሚባሉ ሁለት ታዳጊ ቀበሌዎች በውስጧ ይገኛሉ (Abewa, 2021)፡፡ የወረዳዋ ማኅበረሰብ ሃይማኖት በሚመለከት አብዛኛው የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት (99.09%) ተከታዮች ሲሆኑ፣ የፕሮቴስታንት(0.039%) እና የእስልምና(0.01%) እምነት ተከታዮችም ይገኛሉ (በባሶ ሊበን ወረዳ ባ/ቱ ጽ/ቤት በባህል እሴቶችና ኢንዱስትሪ ልማት ቡድን የተዘጋጀ)፡፡

‹‹ባሶሊበን›› የሚለው መጠሪያ በአጼ ሱስኒዮስ ዘመነ መንግስት በኦሮሞ መስፋፋት ወቅት ‹‹ባሶ›› የተባለ ግለሰብ ከኦሮሚያ ክልል ወደ ጎጃም (አማራ ክልል በሚገኝ ቦታ) መጥቶ በመስፈሩ ምክንያት አሁን ወረዳዋ ለምትጠራበት ቃል መነሻ ሆኗል፡፡ ‹‹ባሶ ሊበን›› የሚለው የሁለት ጥምር ቃል ውጤት ሲሆን ‹‹ባሲ›› ማለት ቀርቃዛ ሲሆን ‹‹ሊበን›› ደግሞ አስመጣ ማለት ነው፡፡ ጥምር ቃሉ ሲተረጎም ‹‹ቀርቃዛ አስመጣ›› የሚል ትርጉም አለው፡፡ ወረዳዋ ጥምር ቃሉን በመክፈል የአካባቢውን መልክዓምድራዊ አቀማመጥ መነሻ በማድረግ በየዳ ወንዝ አካላይነት በወንዙ በስተ ምዕራብ በኩል ያለውን የወረዳዋን ክፍል ባሶ ሲለው በስተ ምስራቅ ያለውን ደግሞ ሊበን ብሎ

ይጠራዋል፡፡ ይህ ቃል የወረዳዋ መጠሪያ በመሆን እስከ አሁን ያገለግላል (Abewa, 2021)፡፡

የወረዳዋ ምስራቅ ክፍል በሊበን በኩል (ቤተ ንጉስ) በወቅቱ ለነበሩ ነገስታት ማረፊያ ነበረች፤ በወቅቱ ንጉስ ተክለሀይማኖት እና ሉዑል ራስ ኃይሉ ወደ ሸዋ በሄዱበት ወቅት ማረፊያ ካደረጓት ነገሥታት መካከል ይጠቀሳሉ፡፡ በተጨማሪም የወረዳዋ ዋና ከተማ የጁቤ የባሪያ ንግድ መዲና እንደነበረችም ይነገራል (Abewa, 2021) እና የባሶ ሊበን ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ፅ/ቤት፣ ባህልና ኪን፣ 2009)፡፡

የባሶሊበን ማኅበረሰብ የመንጻትና መርከስ እሳቤዎች የሚገለጥባቸው የተለያዩ ከበራዊ ሥርዓቶች ያሏቸው ሲሆን፣ በዚህ ጥናት ከርኩሰት ክስተቶች የመንጻት እሳቤን ለማሳየት የ ‹‹ግስ›› ከበራዊ ሥርዓት ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡ ‹‹ግስ›› ማለት በተጠኚው ማኅበረሰብ አውድ ቡድናዊነትን ማስጠበቂያ፣ የሚያሰባስብ ሥርዓት፣ ቡድናዊ ንጽሕና ለማግኘት ዕምነት የሚጣልበት ሥርዓት ማለት ነው፡፡ የከበራ ሥርዓቱ በሽታና መቅሰፍት በተከሰተ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በየዓመቱ በግንቦት ወር የሚከወን እና እንደአስፈላጊነቱ ደግሞ ጥቅምት ወር ላይ የሚተገበር ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የባሶሊበን ማኅበረሰብ የ "ግስ ሥርዓትን" በመጠቀም ከርኩሰት ክስተቶች ለመንጻት እንዴት እንደሚከውን ይመረምራል፡፡

## የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት መነሻ ምክንያት፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በባህል ጥናትም ሆነ በሌሎች የትምህርት ዘርፎች፣ የርኩሰትና የመንጻት ጽንሰ-ሐሳብን ማዕከል ያደረጉ ጥናቶች አለመኖራቸው ነው። ምንም እንኳን ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው አንዳንድ ጥናቶች ቢኖሩም፣ ርዕሰ ጉዳዩን በዋናነት አይመለከቱም። ለምሳሌ፣ ድርብ-ወርቅ (2007) በጉምዝ ብሔረሰብ የሕይወት ዑደት ሽግግሮች ላይ ባደረገችው ጥናት፤ አበበ (2013) ‹‹የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት ክወና (ድግስ ጋሕጃ) ትንተና በጉምዝ ብሔረሰብ ተተኳሪነት››፣ እንዲሁም ሰይድ (2012) ‹‹የወር አበባ የሕይወት ዑደት ሽግግር ሥርዓት በመንጌ ወረዳ በፋኩምኩም ጎሳ›› ባጠኑት ጥናት የወር አበባ ፍሰትን ተከትሎ የሚፈጸሙ የማግለል ሥርዓቶች ከርኩሰት ጋር የተያያዙ መሆናቸውን በንዑስ ርዕስነት ዳስሰዋል። ይሁንና የእነዚህ ጥናቶች ዋነኛ ትኩረት ርዕሰ ጉዳዩ ባለመሆኑ፣ የመንጻት ጽንሰ-ሐሳብን ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንጻር በጥልቀት አይመረምሩም። በተጨማሪም የመርከስና የመንጻት ፍልስፍናን፣

እንዲሁም ለማኅበረሰቡ ያላቸውን ሁለንተናዊ ፋይዳና ትርጉም በዝርዝር አያብራሩም።

በሌላ ማሳያ ደግሞ ከነውር ጋር በተያያዘ ሞላ (2009)፣ ‹‹የነውር እሳቤ በሊቦ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እምነት›› በሚል ርዕስ ባጠኑት ጥናት ክርስትና ያልተነሳ ህጻን ከቤተክርስቲያን አጥር ግቢ ውስጥ መቅበርና ተስካር ያላወጣ ሰው በሌሎች ተስካር መገኘት ርኩሰት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ይበልጣል (2015) ደግሞ ‹‹የወር አበባ እና የወሊድ ነውር እሳቤን በቤንች ማኅበረሰብ›› ባጠናው ጥናት ወላድ ሴት ሳትነጻ ባለቃልቻን ማየት ነውርነቱን ጠቁሟል፡፡ እንዲሁም አያል (2011) የነውር እሳቤ ከልማዳዊ ህግ አንጻር ባጠናችው ጥናት ከሃይማኖታዊ ህግ ጋር በተገናኘ የሚያረክሱ እንስሳትን መብላት ነውርና የሚያረክሱ መሆናቸውን በጨረፍታ ጠቅሳለች፡፡

እነዚህና ሌሎች ከአድርግ አታድርግ ህግ ጋር የተያያዙ ጥናቶች በንዑስ ጉዳይነት የሰዎችን የርኩሰት ተግባር የሚጠቁሙ እንጂ ከርኩሰቱ የሚነጹበት ማኅበረ-ባህላዊ መንገድ እና የወል እውቀት በመርከስና በመንጻት ቲዎሪና ጽንስ ሐሳቦች ተገናዝበው አልተጠኑም፡፡ ሌላኛው ከዕመነታዊ ከበራዎች ጋር በተያያዘ ፀዳለ (2007) ‹‹በቀይት ንዑስ ወረዳ የሚከወኑ ሃገረሰባዊ እምነቶችና ስርዓተ ክዋኔያቸው›› በሚል ርዕስ ባጠናችው ጥናት ከመናፍስት ቁጣ ለመጠበቅ የሚከወኑ ዕምነቶችን ገልጻለች፡፡ ይህ ጥናት አውዳዊ ክዋኔውና በመንጻትና መርከስ ቲዎሪ በመቀንበብ ከመጠናቱ ባሻገር የሥርዓቱ ደንብና አተገባበሩ የተለያዬ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም Antohin (2014) ‹‹Expressions Of Sacred Promise: Ritualand Devotion In Ethiopian Orthodox Praxis›› በሚል ርዕስ በስነሰብ መስክ ያጠኑት ጥናት በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት አምልኳዊ ሥነሥርዓቶች በሰዎች ማኅበራዊ መስተጋብር እንደሚገለጡ በማሳየት፣ የአምላክን ትዕዛዝ መጣስ የጽድቅና የኃጢያት ተግባር ማሳያ ስለመሆኑ ጠቁመዋል፡፡ ይህ ተግባር ከንጽሕናና ርኩሰት ጽንስ ሐሳብ ጋር የሚገናኝ ቢሆንም ጥናቱ በፎክሎራዊ እሴት ትኩረት ተደርጎ የተመረመረ አይደለም፡፡ በሌላ መንገድ፣ Zesu (2014) ‹‹The Sacred and the Profane - Environmental Anthropology of Ethiopian Orthodox Christianity›› በሚል ርዕስ ባጠኑት ጥናት በትግራይ እንደርታ ወረዳ ያሉ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ቦታዎች ብዝሃ ተፈጥሯዊ ሃብቶች የሚገኙባቸውና ከቦታዎች ቅድስና ጋር የተገናዘቡ ስለመሆናቸው እንደሚታመን ያስረዳሉ፡፡ እነዚህን ሃብቶች መጠበቅ የእሴት መገለጫ ከመሆን ባለፈ ርኩሱን ከቅዱሱ ተግባር ለመለየት የሚረዱ

ስለመሆናቸው ገልጸዋል፡፡ ከላይ የቀረቡት ጥናቶች የመንጻትና መርከስን ጽንስ ሐሳብ በቀጥታ የማያሳዩ ከመሆናቸው ባሻገር ባህላዊና ማኅበራዊ ጉዳዩችን በጥልቀት የመረመሩ አይደሉም፡፡ ይኸ ደግሞ አንባቢው ጉዳዩን በራሱ ችሎ ለመረዳት እንዲቸገር ያደርገዋል። ስለሆነም፣ ይኸ ጥናት፣ ይህንን አካዳሚያዊ ክፍተት በመሙላት በጽንሰ-ሐሳቡ ዙሪያ ጥልቅ ግንዛቤ ለመስጠት ያለመ ነው።

### የጥናቱ ዓላማ(ዎች)

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በባሶሊበን ማኅበረሰብ ዘንድ የ"ግስ" ሥርዓትን በመተግበር ከርኩሰት የመንጻት እሳቤን መመርመር ነው። ዝርዝር ዓላማዎች ደግሞ፦ በ ‹‹ግስ›› ሥርዓት በመጠቀም ማኅበራዊነትን የማስጠበቅ እሴትን መግለጽ፤ በ ‹‹ግስ›› ሥርዓት የሚተገበሩ ደንቦችን መመርመር እና በ ‹‹ግስ›› ሥርዓት የሚወገዱ የርኩሰት ክስተቶችና የሚያነጹ ተግባራትን ማሳየት፣ የሚሉት ናቸው፡፡

### የጥናቱ ጠቀሜታ

በ“ግስ” ሥርዓት አውድ የመንጻት እሳቤን በመጠቆም ከመርከስ ተግባራት ለመጠበቅ የሚረዱ ማኅበራዊ ደንቦችና እሴቶች በጽሑፍ እንዲሰነዱ በማድረግ ረገድ ለማኅበረሰቡ ዕውቀት ቀጣይነት አስተዋጾ ሊያበረክት ይችላል፡፡ በተጠኚው ማኅበረሰብ ዘንድ የሚከሰቱ የርኩሰት ክስተቶች የሚያስከትሏቸውን ተጽዕኖዎች በመጠቆም ንጽሕናን ለመጠበቅ ሰዎች የሚከለከሉባቸውን ተግባራት ለማስረዳት እና በግስ ሥርዓት መንጻት የሚተገበርበትን ዓላማ ለማስገንዘብ ይረዳል፡፡

## ጽንሰ ሐሳባዊ ማሕቀፎች

ይኸ የክለሳ ድርሳናት ግምገማ እና ጽንሰ-ሐሳባዊ ማሕቀፍ፣ "መንጻት፣ ርኩሰት/መርከስ፣ ሥርዓት፣ ማኅበራዊ ትስስር፣ ማኅበራዊ ደንቦች/ሕጎች እና ባህላዊ እሴቶች" የሚሉትን ዋና ዋና ጽንሰ-ሐሳቦች፣ በተግባራዊ-መዋቅራዊነት (Structural-Functionalism) እና በመንጻትና መርከስ ንድፈ ሐሳብ (Purity and Pollution Theory) መነጽር በመቃኘት ያቀርባል። እነዚህ ጽንሰ-ሐሳቦች የማኅበራዊ ሥርዓቶችን፣ የቡድን ግንኙነቶችን እና የባህል እሴቶችን ለመረዳት መሠረታዊ እንደሆኑ ይተነትናል። በተለይም፣ የኢትዮጵያን ባህላዊ አውድ በሚመለከቱ ጥናቶች አማካኝነት ጽንሰ-ሐሳቦቹ እንዴት እንደተፈተሹ እና ለማኅበረሰቦች ያላቸውን ፋይዳ ያብራራል።

## መንጻት (Purification) እና ርኩሰት/መርከስ (Impurity/Defilement)

የመንጻትና የርኩሰት ጽንሰ-ሐሳቦች የማኅበረሰብ ባህላዊና ማኅበራዊ ሥርዓት ምሰሶዎች ናቸው። ሜሪ ዳግላስ (Douglas) በታዋቂው ሥራዋ "Purity and Danger" (1966) ላይ እንደገለጸችው፣ ርኩሰትና ንጽሕና በቀላሉ ከአካላዊ ንጽህና ጋር ብቻ የተያያዙ ሳይሆኑ፣ የማኅበረሰቡን ዓለም እይታ (cosmology) የሚያንፀባርቁ ጥልቅ ምድቦች ናቸው። ዳግላስ ርኩሰትን "ሥርዓትን ያጣ ጉዳይ" (matter out of place) በማለት ትገልጸዋለች፤ ይህም ማለት ከቦታው ወይም ከሚጠበቀው ሥርዓት የወጣ ማንኛውም ነገር ርኩስ ተብሎ እንደሚፈረጅ ትገልጻለች። ስለዚህ፣ ርኩሰት ከማኅበራዊ ሥርዓት መጣስ፣ ከአደጋ፣ ከውኀንብር እና ከሞት ጋር ይያያዛል (Douglas, 1966)። መንጻት ደግሞ፣ ይህን ሥርዓት የለሽ ሁኔታ ወይም ርኩሰትን በማስወገድ ወደ ቀድሞው ሚዛንና ሥርዓት የመመለስ ሂደትን ይመለከታል።

## ክብረ በዓል (Ritual)

ክብረ በዓላት፣ የመንጻትና የመርከስ ጽንሰ-ሐሳቦችን በተግባር ለመተርጎም የሚያገለግሉ ቁልፍ ማኅበራዊና ባህላዊ መሣሪያዎች ናቸው። ራድክሊፍ-ብራውን (Radcliffe-Brown,1952) በ ‹‹Structure and Function in Primitive Society›› እንደሚያብራሩት፣ ክብረ በዓላት የማኅበረሰቡን የጋራ ሥነ-ምግባር (moral sentiments) የሚገልጹና የሚያጠናክሩ ናቸው። የክብረ በዓላት መኖር ማኅበራዊ መዋቅርን በመጠበቅ እና ግለሰቦችን ከቡድን ጋር በማዋሃድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ቪክቶር ተርነር (Turner,1969) በ"The Ritual Process" ውስጥ የሽግግር ሥርዓቶችን (rites of passage) ሲያብራራ፣ ሥርዓቶች ግለሰቦችን ከአንድ ማኅበራዊ ሁኔታ ወደ ሌላ በማሸጋገር ረገድ ያላቸውን ኃይል አሳይቷል። እነዚህ ሥርዓቶች የመንጻት ተግባራትንም ሊያካትቱ ይችላሉ። ቫን ጄኔፕ (Van Gennep,1960) በ "The Rites of Passage" ደግሞ ሽግግርን በሦስት ደረጃዎች ይከፍላሉ፤ መለየየት (separation)፣ የሽግግር ደረጃ (liminality) እና መቀላቀል (incorporation)። በሽግግር ደረጃ ላይ የመንጻት ሥርዓቶች ወሳኝ ሲሆኑ፣ ግለሰቡን ከቀድሞው ሁኔታ "ርኩሰት" በማንጻት ለአዲሱ ሁኔታ "ንጽሕና" ያዘጋጃሉ።

በኢትዮጵያ አውድ ውስጥ፣ አስፐን (Aspen, 1997) በ "Amhara Traditions of Knowledge: Spirit Mediums and Their Clients" ላይ እንደሚያሳየው፣ መንፈሳዊ ሥርዓቶች እና የመንፈስ ባለቤቶች (spirit mediums) ርኩሰትን በማስወገድ እና መንጻትን በማስፈን ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። እነዚህ ሥርዓቶች የማኅበረሰቡን ጤና፣

ከብቶችን እና ሰብሎችን ከአደጋ ለመጠበቅ ያለመ አምልኮታዊ ገጽታ ሊኖራቸው ይችላል።

## ማኅበራዊ ትስስር (Social Cohesion)

ማኅበራዊ ትስስር ማኅበረሰብን በአንድነት የሚያቆይ ኃይል ሲሆን፣ ሥርዓቶች ይህንን ትስስር ለመገንባትና ለማጠናከር ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። በተግባራዊ-መዋቅራዊነት ንድፈ ሐሳብ መሠረት፣ ሥርዓቶች የጋራ እሴቶችን፣ እምነቶችን እና ደንቦችን በመድገም የማኅበረሰቡ አባላት የአንድ ቡድን አካል እንደሆኑ እንዲሰማቸው ያደርጋሉ (Radcliffe-Brown, 1952)። ርኩሰትን የማንጻት ሥርዓቶች፣ በተለይም የጋራ ርኩሰት በሚታይበት ጊዜ፣ ማኅበረሰቡን በጋራ ዓላማ ዙሪያ በማሰባሰብ የጋራ ዕጣ ፈንታ እንዳላቸው እንዲገነዘቡ ያደርጋል። የጋራ ችግሮች ሲከሰቱ (እንደ ወረርሽኝ በሽታዎች ወይም የተፈጥሮ አደጋዎች)፣ የጋራ የመንጻት ሥርዓት መከወን የቡድን ስሜትን ያጠናክራል እና የአብሮነት እሴትን ያሳድጋል (Douglas, 1966)።

ፓንክረስት (Pankhurst, 1990) በ "A Social History of Ethiopia" ላይ የኢትዮጵያን ማኅበራዊ መዋቅሮች ሲገልጽ፣ ቤተሰብን፣ ሃይማኖትን እና ሌሎች ባህላዊ ተቋማትን ጨምሮ የተለያዩ ሥርዓቶች ማኅበራዊ ትስስርን እንዴት እንደጠበቁ ያብራራል። የመንጻት ሥርዓቶችም ይኽንን ትስስር በማደስና በማስጠበቅ ረገድ ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው መገመት ይቻላል።

## ማኅበራዊ ደንቦች/ሕጎች (Social Norms/Rules)

ማኅበራዊ ደንቦች/ሕጎች አንድ ማኅበረሰብ እንዴት መኖር እንዳለበት የሚወስኑ መመሪያዎች ሲሆኑ፣ የመንጻትና የርኩሰት ጽንሰ-ሐሳቦች እነዚህን ደንቦች በመቅረጽ ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። የርኩሰት ጽንሰ-ሐሳብ፣ ሰዎች ሊያደርጉት የሚገባውን (ንጹሕ የሆነውን) እና ሊያደርጉት የማይገባውን (ርኩስ የሆነውን) በመለየት፣ የማኅበራዊ ባህሪን ይቆጣጠራል (Douglas, 1966)። ደንቦችን መጣስ እንደ ርኩሰት ሊቆጠርና ማኅበራዊ ቅጣትን ሊያስከትል ይችላል፣ ይህም ግለሰቡን ከማኅበረሰቡ ማግለልን ያካትታል። የመንጻት ሥርዓቶች ደግሞ፣ የተጣሱ ደንቦችን ለማስተካከል እና ግለሰቡን ወደ ማኅበራዊ ደንብ ለመመለስ የሚያስችሉ መንገዶችን ያቀርባሉ።

በአማራ ባህል ውስጥ፣ እንደ ሊቪን (Levine, 1965) ገለጻ፣ የሥነ-ምግባርና የባህርይ ደንቦች በጥብቅ የሚጠበቁ ሲሆን፣ ከእነዚህ ደንቦች ማፈንገጥ ማኅበራዊ ውግዘትን ሊያስከትል ይችላል። የመንፈስ

ባለቤቶች (spirit mediums) የሚያቀርቧቸው የመንጻት ሥርዓቶች፣ አንዳንድ ጊዜ ማኅበራዊ ደንቦችን በመጣስ የተከሰቱ ችግሮችን ለመፍታትና ግለሰቦችን ወደ ትክክለኛው መንገድ ለመመለስ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ (Aspen, 1997)።

## ባህላዊ እሴቶች (Cultural Values)

ባህላዊ እሴቶች ማኅበረሰብ የሚመራባቸው የጋራ መርሆዎች፣ እምነቶች እና የሥነ-ምግባር መመዘኛዎች ናቸው። የመንጻትና የርኩሰት ጽንሰ-ሐሳቦች በቀጥታ ከእነዚህ እሴቶች ጋር የተቆራኙ ናቸው። ንጹሕ ተብሎ የሚታሰበው ነገር የማኅበረሰቡን አዎንታዊ እሴቶች የሚያንፀባርቅ ሲሆን፣ ርኩስ ተብሎ የሚታሰበው ደግሞ በእሴቶቹ ላይ ስጋት የሚፈጥር ነው። ሥርዓቶች ደግሞ እነዚህን ባህላዊ እሴቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍና ለማጠናከር ይረዳሉ (Radcliffe-Brown, 1952)። የጋራ የመንጻት ሥርዓቶችን መከወን፣ ማኅበረሰቡ ለአንድነት፣ ለጤና፣ ለሰላም እና ለሥነ-ምግባራዊ ንጽሕና የሚሰጠውን ዋጋ ያሳያል።

በኢትዮጵያ፣ እንደ ፓንክረስት (Pankhurst, 1990) እና ሜሲንግ (Messing, 1957) ባሉ ምሁራን ጥናቶች እንደተገለጸው፣ ቤተሰብን ማክበር፣ ማኅበራዊ ትስስርን መጠበቅ፣ እና መንፈሳዊ ሥርዓቶችን ማክበር ዋነኛ ባህላዊ እሴቶች ናቸው። የመንጻት ሥርዓቶችም እነዚህን እሴቶች በመጠበቅ፣ በማደስ እና ከማንኛውም "ርኩሰት" በመከላከል የማኅበረሰቡን ህልውና ለማስጠበቅ ያገለግላሉ።

## መዋቅራዊ-ተግባራዊነት (Structural-Functionalism)

ይህ ንድፈ ሐሳብ፣ ማኅበረሰብን እንደ አንድ ወጥ አካል የሚያይ ሲሆን፣ እያንዳንዱ የማኅበረሰቡ ክፍል የራሱ የሆነ ተግባር ያለውና የሌሎችን ክፍሎች ለመደገፍ የሚሠራ እንደሆነ ይገለጻል (Brown, 2013); Wandi et al., 2021)። በዚህ ማሕቀፍ፣ የ"ግስ" ሥርዓት በባሶሊበን ማኅበረሰብ ውስጥ ያለውን ማኅበራዊ ትስስር እና የጋራ እሴቶችን ለመጠበቅ የሚፈይደውን ተግባር ይፈተሻል። ሥርዓቱ እንደ አንድ ማኅበራዊ ተቋም፣ በቡድኑ ውስጥ ያለውን የጋራ ስምምነትና ተጠቃሚነትን እንዴት እንደሚያጠናክር፣ እንዲሁም የማኅበረሰቡን የአብሮነት እሴት ከግለሰባዊ ምግባር ጉድለቶችና ከውጫዊ አደጋዎች ለመጠበቅ ያለውን ሚና ይመረምራል። ለምሳሌ፣ በ"በረት አባት" የሚከናወኑ የኃላፊነት ተግባራት (እንደ መዋጮዎችን መቆጣጠር፣ ስምምነትን ማስጠበቅ፣ እርቅ ማስፈን) የማኅበረሰቡን መዋቅርና ተግባር እንዴት እንደሚያጠናክሩ ይተነትናል (Sato, 2011)።

### የመንጻትና መርከስ ንድፈ ሐሳብ (Purity and Pollution Theory)

ይህ ንድፈ ሐሳብ በሥነ-ሰብ ተመራማሪዋ ሜሪ ዳግላስ ( Douglas, 1966) በስፋት የተብራራ ሲሆን፣ መንጻትና መርከስ አካላዊ ላይ ብቻ የተገደቡ ሳይሆኑ በጥልቅ ማኅበራዊና ባህላዊ ሥርዓቶች የሚታዩ መሆናቸውን ያብራራል (Douglas, 2003)። ዳግላስ "የመርከስ ጽንሰ ሐሳብ ካለ ማኅበራዊ ሥርዓት አለ" በማለት፣ መርከስ፤ ሥርዓት ከማጣት፣ ቅርጽ ከሌለው፣ ከሞት እና ከብክለት ስሜት ጋር የሚቆራኝ መሆኑን ትጠቁማለች (Blidstein, 2017; Feder, 2021)። በዚህ ማዕቀፍ፣ ጥናቱ በ"ግስ" ሥርዓት አማካኝነት የሚተገበሩ ደንቦችን፣ የሚወገዱ የርኩሰት ክስተቶችን (እንደ ተላላፊ በሽታዎች፣ የተፈጥሮ አደጋዎች፣ ማኅበራዊ ጥላቻና ስርቆት) እና የሚያነጹ ተግባራትን ይመረምራል። ለምሳሌ፣ ደምን በመርጨት የሚከናወነው መንጻት ከበሽታና ከተፈጥሮ አደጋዎች የመጠበቅ ተግባርን፣ እንዲሁም በሥርዓቱ ለመሳተፍ የሚያስፈልጉት ሞራላዊና ሥነ-ምግባራዊ መስፈርቶች የማኅበረሰቡን የሥነ-ምግባር ንጽሕና እንዴት እንደሚያስጠብቁ ይተነትናል (Gray et al., 2022; Cossu, 2024)። የ"ግስ" ሥርዓትን ደንቦች ማክበር የንጽሕና መገለጫ ሲሆን፣ ደንቡን አለመጠበቅ ደግሞ ርኩሰት ተደርጎ እንደሚታይ ይህ ማዕቀፍ የጥናቱ መረጃዎችን ለመተርጎም ይረዳል።

## የአጠናን ስነዘዴ

ይኸ ጥናት በማኅበረ-ባህላዊ ክስተቶች ውስጥ ያለውን ጥልቅ ትርጉም ለመረዳት ያለመ እንደመሆኑ፣ በአይነታዊ ምርምር (qualitative research) አካሄድ ላይ የተመሠረተ ነው። በተለይም፣ እንደ **ክሊፈርድ ጊሪቴዝ (Clifford Geertz)** አገላለጽ፣ ባህልን እንደ "የትርጉም ድር (web of significance)" በመቁጠር፣ የ‹‹ግስ›› ሥርዓትን ተፈጥሯዊ በሆነው ማኅበራዊ መቼቱ ውስጥ ለመተርጎም የሚያስችለውን የኢትኖግራፊያዊ (ethnography) የምርምር ንድፍን ተከትሏል። የጥናቱ አካባቢ የሆነው ባሶ ሊበን ወረዳ እና በውስጡ የተካተቱት አምስት ቀበሌዎች (ኮርክ፣ የላምገንጅ፣ ልምጭም፣ ደን እና የጁቤ 01) የተመረጡት በዓላማ ተኮር ናሙና (purposive sampling) ስልት ነው።

ይህ አካሄድ፣ ማይክል ኩዊን ፓተን (Michael Quinn Patton) እንዳስቀመጡት፣ ጥልቅና የበለጸገ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ "ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸውን ተሳታፊዎችንና ቦታዎችን (information-rich cases)" ለመምረጥ ያለመ ነው። የመረጃ ሰጪዎችን ለመለየት ደግሞ ጉዳዩን በቅርበት የሚያውቁ ቁልፍ ሰዎችን እንደ መነሻ በመጠቀም

ወደ ሌሎች ተሳታፊዎች ለመድረስ የሚያስችለው አመልካች/ቅብብሎሽ (snowball) ናሙና ጥቅም ላይ ውሏል። ይኸም በሥርዓተ-ፆታ፣ በትምህርት ደረጃ እና በእድሜ የተለያየ ተዋፅኦ ያላቸውን የማኅበረሰቡ አባላት በማካተት ሰፋ ያለ አመለካከት ለመያዝ አስችሏል።

የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎች የተሰበሰቡት የምርምሩን ተዓማኒነት ለማረጋገጥ በሚረዳውና በኖርማን ዴንዚን (Norman Denzin) በስፋት በተብራራው የማመሳከር (triangulation) መርህ ላይ ተመስርቶ ነው። በዚህም መሰረት፣ ምልከታ (observation)፣ ጥልቅ ቃለ-መጠይቅ (in-depth interview) እና ቡድን ተኮር ውይይት (focus group discussion) የተሰኙ ሦስት የተለያዩ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። ተመራማሪዋ በ‹‹ግስ›› ክዋኔ ወቅት በሚከናወኑ ተግባራት ላይ በቀጥታ በመሳተፍ (participant observation) የውስጥ አዋቂ እይታን ለማግኘት የሞከረች ሲሆን፣ በተመሳሳይ ከሂደቱ በመውጣት ሁኔታዎችን ከውጭ በመመልከት (non-participant observation) ሰፋ ያለ እይታን አግኝታለች።

ከሽማግሌዎችና ከሌሎች የማኅበረሰቡ አባላት ጋር የተደረጉት ጥልቅ ቃለ-መጠይቆች ስለ ሥርዓቱ ማኅበራዊ ፋይዳ፣ የንጽህና ደንቦችና የርኩሰት ጽንሰ-ሐሳቦች ጥልቅ ግንዛቤ ለማግኘት አስችለዋል። በተጨማሪም፣ በቡድን የተካሄዱት ውይይቶች በግል ቃለመጠይቅ ያልተገኙ የማኅበረሰቡ የጋራ አመለካከቶችን ለማሰባሰብና የተገኙ መረጃዎችን ለማጠናከር ረድተዋል። ይህ የመረጃ አሰባሰብ ሂደት የቀጠለው፣ ግሌዘር እና ስትራውስ (Glaser and Strauss) በግራውንድድ ቲዎሪ (Grounded Theory) ውስጥ እንዳስቀመጡት፣ አዲስ መረጃ መገኘት አቁሞ የተሰበሰበው መረጃ መደጋገም ሲጀምር በሚደረስበት የመረጃ ሙሌት (data saturation) ደረጃ ድረስ ነበር።

የተሰበሰበው መረጃ የተተነተነው የክዋኔ ሂደቶችን በዝርዝር ለማቅረብ በገላጭ ትንተና (descriptive analysis) እና ከበስተጀርባ ያሉትን ፍልስፍናዎች፣ እሴቶች እና ትርጉሞች ለመፈተሽ በይዘት ትንተና (content analysis) ነው። የትንተናው ማዕቀፍም በሥነ-ሰብ ጥናት (anthropology) ውስጥ በሰፊው የሚታወቁትን ሁለት አተያዮች አካቷል። የመጀመሪያው፣ እንደ ሄኔዝ ፓይክ (Headland et al.,1990) ገለጻ፣ የማኅበረሰቡን አባላት የራሳቸውን አመለካከትና ትርጓሜ ማዕከል ያደረገው ውስጣዊ/emic እይታ ሲሆን፣

ሁለተኛው ደግሞ በአጥኚዋ አካዳሚያዊ እውቀትና እይታ የተቃኘው **ውጫዊ/etic እይታ** ነው። ይህ ድርብ አካሄድ ክስተቱን

ከሁለት አቅጣጫዎች ለመረዳት አስችሏል። በምርምሩ ሂደት ውስጥ የጥናት ሥነ-ምግባር ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ሲሆን፣ ሁሉም ተሳታፊዎች ስለ ጥናቱ ዓላማ በቂ ግንዛቤ አግኝተው በፈቃደኝነት እንዲሳተፉ (informed consent) ተደርጓል። በመጨረሻም፣ እንደ ‹‹ግስ››፣ ‹‹ርኩሰት›› እና ‹‹ንጽህና›› ያሉ ቃላት ያላቸውን ጥልቅ ማኅበረ-ባህላዊ ትርጉም በመተንተን፣ ጽንሰ-ሐሳባዊ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡

## የመረጃ ትንተና

### በግስ ሥርዓት ርኩሰትን የማንጻት እሳቤ ትንተና

በዚህ ክፍል የ"ግስ" ሥርዓትን በመጠቀም ከርኩሰት የማንጻት እሳቤውን የሚያሳዩ መረጃዎች የቀረቡበት ሲሆን፣ በግስ ሥርዓት ማኅበራዊነትን የማስጠበቅ እሴት፣ በግስ ሥርዓት የሚተገበሩ ደንቦች እና የርኩሰት ክሰተቶችና የሚያነጹ ተግባራት የተተነተኑበት ነው፡፡

### በ ‹‹ግስ›› ሥርዓት ማኅበራዊነትን የማስጠበቅ እሴት

እሴት ለአንድ ማኅበረሰብ መገለጫ የሆነና የጋራ አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ እምነት እና ፍልስፍና የሚታይበት ሲሆን፣ ማኅበረሰቡ በቡድናዊ አብሮነቱ ውስጥ የሚመራባቸው የተለያዩ ማኅበራዊ ደንቦችና ህጎችን ይቀርጻል፡፡ Boudon (2017) ማኅበራዊ እሴቶች አንድ ማኅበረሰብ በተለያዩ ምክንያቶች የመሰረታቸው የሃገረሰባዊ እምነት ውጤቶች ሲሆኑ፣ ለማኅበራዊ አንድነት ምስረታ የሚረዱና ከትውልድ ትውልድ የሚያስተላልፏቸው የጥሩና መጥፎ ተግባራት መለያ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

በመሆኑም፣ በባሶሊበን ማኅበረሰብ ዘንድ ማኅበራዊ ትስስራቸውን ሊያናጉ የሚችሉና በግለሰቦች ምግባር የሚገለጡ የርኩሰትና ንጽሕና እሳቤዎች አሏቸው፡፡ በተጠኚው ማኅበረሰብ ዘንድ የአንድ ሰው ንጽሕና ሞራላዊ መሰረቱ የሚገለጠው በማኅበራዊ ትስስር ውስጥ ቡድኑ በሚያምንበት ሥርዓት መታዘዝና መገዛት ሲችል ነው፡፡ ስለሆነም፣ ለቡድናዊ ሥርዓቱ ባለመገዛታቸው የሚከሰቱ የርኩሰት አደጋዎች ከማኅበራዊ አብሮነት እንዲነጠሉ ያደርጋል፣ በዚህ ምክንያት ደግሞ የሚከሰቱ ግለሰባዊ ችግሮችን (የጤና ማጣት፣ ከመረዳዳት እሴት የመነጠል እና ከእድር የመገለል) ለመግታትና ወደ ማኅበራዊ ሥርዓቱ ለመመለስ የሚረዱቸውን ሥርዓቶች ይተገበራሉ፡፡

Douglas (2003) እና **Cossu** (2024) በሞራል መርከስ የቡድኑን የጥሩ ምግባር መገለጫ አለመፈጸምን የሚገልጽና ከማኅበራዊ ደንብ ጥሰት ጋር የተያያዘ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በተጠኚው ማኅበረሰብ አውድ፣ "ርኩሰት" ማለት ቂም፣ ጥላቻ፣ በሽታ፣ ሰብል መውደም፣ የቤት እንስሳት መሞት ወይም የተፈጥሮ አደጋዎች ሊሆኑ ይችላሉ (አቶ እንየው መጋቢት 21፣ 2017 በቃለመጠይቅ)። እነዚህ ችግሮች የማኅበረሰቡን አብሮነትና መረጋጋት የሚያናጉ በመሆናቸው እንደ "መርከስ" ያስቆጥራሉ።

በባሶሊበን ማኅበረሰብ ውስጥ፣ የተለያዩ የተፈጥሮ እና ማኅበራዊ አደጋዎችን ለመከላከል ሁሉም ሰው የተወሰኑ የሥነ-ምግባር እሴቶችን ማክበር አለበት የሚል ጠንካራ እምነት አለ። ለተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት የእሴት መጣስ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ለዚህም ነው ማኅበረሰቡ የቡድን ግንኙነትን ለማጠናከር እና እንደ ርኩሰት የሚታዩ ክስተቶችን እና ድርጊቶችን ለማንጻት የአምልኮ ሥርዓቶችን፣ በተለይም የ"ግስ" ሥርዓትን የሚጠቀመው።

"ግስ" የሚለው ቃል በዚህ ማኅበረሰብ ውስጥ ቡድንን ለመጠበቅ እና ለማዋሀድ የታመነበትን ሥርዓት ያመለክታል፡፡ ይኸም የጋራ ንጽሕናን ያረጋግጣል። የ"ግስ" ሥርዓት የሚተገበረው ማኅበረሰቡን ለማንጻት እና በማኅበራዊ ትስስር ላይ ርኩሰት ሊያስከትሉ ከሚችሉ ክስተቶች ለመጠበቅ በማሰብ ነው። ይህ ሥርዓት በክዋኔ የሚገለጽ ሲሆን፣ ስሙም የጋራ መንጻት እምነት የጋራ መጠሪያ ሆኖ ያገለግላል።

በዋነኛነት፣ ይኽ የከበራ ሥርዓት "ግስ" በመባል በሠፊው ቢታወቅም፣ አንዳንድ የማኅበረሰብ ክፍሎች ግን በተለያዩ ስሞች ይጠሩታል። ይኽ የከበራ ሥርዓት በቆላማ አካባቢዎች አልፎ አልፎ "ዋሪጋ" ተብሎ ሲጠራ፣ በደጋማ እና ወይና ደጋ አካባቢዎች ደግሞ "ግስ" የሚለው ቃል ሳይተካ ጥቅም ላይ ይውላል። በተጨማሪም ከመረጃ ሰጪዎች (በግንቦት 5 ቀን 2017 ከተደረገ ቃለ መጠይቅ) በተገኘ መረጃ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ "ፍራጅ" በሚል መጠሪያ የሚከውኑት እንዳሉም ያብራራሉ። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ የተለያዩ ስሞች ቢኖሩም፣ "ግስ" በማኅበረሰቡ ውስጥ በብዛት ጥቅም ላይ የዋለው ቃል በመሆኑ፣ ለዚህ ጥናት ተመርጧል።

የግስ ሥርዓት "ቂምና ጥላቻን ለማስወገድ፣ እርቅን ለማስፈንና በማኅበረሰቡ ዘንድ አብሮነትን ለመገንባት" የሚተገበር ሥርዓት መሆኑ፣ ማኅበራዊ መታወክ የሚፈታባቸው እና ወደ ነበረ ሠላም የመመለሻ ማኅበራዊ ጥበቦች እንዳሉ ያሳያል። ማኅበረሰቦች እሴቶቻቸውን፣ ማንነታቸውንና አንድነታቸውን ከጠበቁበት "ንጹህ"

ሁኔታ ሊያበላሹ ወይም ሊያረክሱ ከሚችሉ "ርኩስ" ነገሮች ይለያሉ። ርኩሰት ማኅበራዊ አለመግባባትን፣ በሽታን ወይም የተፈጥሮ አደጋን ሊያመለክት ይችላል። የግስ ሥርዓትም በዚህ መነፅር ሲታይ፣ ዋና ዓላማው ማኅበረሰቡን ከእንደዚህ አይነት ቁጣዎችና አደጋዎች ራስን ለማዳን የሚደረግ ሙከራ መሆኑን ይነግራል።

የግስ ሥርዓት የማኅበረሰቡን መዋቅራዊ ጤንነት የሚገነባና የሚያጠናክር ወሳኝ ማኅበራዊ መተሳሰሪያ ነው። ሥርዓተ ክዋኔው የማኅበረሰቡን ሰላም፣ መረጋጋት እና ዘላቂነት ለማስጠበቅ ወሳኝ የሆኑ ተግባራትን ያከናውናል። የመጀመሪያው፣ ማኅበራዊ ወጥነትንና ትስስርን ለማጠናከር ያገለግላል።ሥርዓቱ የሚከበረው በግለሰብ ሳይሆን በቡድን በመሆኑ፣ ሰዎች ከየቦታው ተሰባስበው የጋራ ሥነ ሥርዓት ሲያካሂዱ፣ የጋራ ማንነታቸውንና አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ ይረዳቸዋል። ይኸ ሂደት የማኅበረሰቡ ትስስር እንዲታደስ እና ትውልድ ከአባቶቹ የወረሰውን እሴት እንዲጠብቅ ያደርጋል። ይኸ ተግባር ማኅበረሰቡን እንደ አንድ አካል አድርጎ ለማቆየት የሚረዳ ሲሆን፣ ከውጭ ወይም ከውስጥ የሚመጡ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ያስችላል።

ሁለተኛው ደግሞ፣ የማኅበራዊ ንፅህናንና ቁጥጥርን ለማስጠበቅም ይገለገሉበታል። የግስ ሥርዓት ዓላማ "በማኅበራዊ አብሮነት ላይ ርኩሰት የሚያስከትሉ ክስተቶችን በመሰባሰብ ለማንጻት" ይጠቅማል። ይኸም ማኅበረሰቡን ከብልሹ ነገሮች፣ ከግጭት እና ከሥነ ምግባር መጓደል ለመጠበቅ የሚያግዝ መቆጣጠሪያ ነው። ይኸ ባህላዊ የቁጥጥር ዘዴ ማኅበራዊ ደንቦችን በማስጠበቅ እና ማኅበራዊ ወንጀሎችን በመከላከል ማኅበረሰቡን ከመበታተንና ተለያይቶ ከመነቋቆር ይጠብቀዋል።

በመጨረሻም፣ ለሥነ-ልቦና ደህንነትም የሚሰጠው ጥቅም አለ። "ግስ" የሚከበረው እንደ ሰብል መውደቅ፣ በሽታ፣ እና የተፈጥሮ አደጋ የመሳሰሉ ያልተጠበቁ ችግሮች እንዳይከሰቱ በመማፀን ነው። በዚህ ሥርዓት ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች ሊደርስባቸው ከሚችል አደጋና ሥነ-ልቦናዊ ስጋት፣ እፎይታና ጥበቃ እንደሚያገኙ እንዲሰማቸው ያደርጋል። ይኸ ደግሞ ለኑሮ የሚያስፈልገውን ተስፋና ሞራል እንዲሁም የጋራ ዕጣ ፈንታና ምኞት ይጨምረዋል። ማኅበረሰቡን ከፍርሃትና ከጭንቀት በመከላከል የስነ-ልቦና ጤንነቱን ያጎለብታል።

የግስ ሥርዓት የሚከበረው ከክረምት ጋር ተያይዞ ከሚመጡ ችግሮች፣ አደጋዎችና በሽታዎች ለመጠበቅ ሲባል ነው። ይህ ሥርዓት፣ "ክረምቱን ከተለያየ አደጋ ተጠብቀን፣ እንኳን በሰላም ለዚህ ደረስን" የሚል የምስጋና መልዕክት ሲያስተላልፍ፣ ማኅበረሰቡ

ከጭንቀትና ከፍርሃት እፎይታ እንዲያገኝ ይረዳል። ሥርዓቱ ለግብርና፣ ለእንስሳትና ለሰው ልጆች ጤና መከበር፣ ለዘር እንዲሆን መማፀን እና ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ ችግሮችን አስቀድሞ ለመከላከል ያለመ መሆኑ፣ የማኅበረሰቡን የስነ-ልቦና ፍላጎት እንደሚያሟላ ያሳያል።

ሥርዓቱ በማኅበረሰቡ ዘንድ ከመቼ ጀምሮ ይከበር እንደነበር ለመረዳት ተጨባጭ መረጃዎች ባይኖሩም “ግስ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣና ረዥም ዘመንን ያስቆጠረ ተስፋን መግዣ እና መቆጣጠሪያ ሥርዓት ነው፡፡ ሰውና ከብቱ ጤና እንዲሆን፣ በሃገሩና በቀዬው ሰላም እንዲሰፍን የምንተገብረው ነው” (ልምጭም ግንቦት 1፣ 2017 በቃለ መጠይቅ) በማለት ይገልጹታል፡፡

የ"ግስ" ሥርዓት በአካባቢው በየዓመቱ በጥቅምት እና በግንቦት ወር የሚከበር ሲሆን፣ ቀናቱ በማኅበረሰቡ ሽማግሌዎች ስምምነት ይወሰናሉ። በግንቦት ወር ውስጥ ይህን ሥርዓት የሚያከብሩበት ምክንያት የእርሻ ወቅት እና የክረምት መጀመሪያ በመሆኑ ነው። በዚህ ጊዜ ሥርዓቱን ማክበር የእርሻውን ዘርፍ፣ እንስሳትንና ሰዎችን ከክረምት ጋር ተያይዘው ከሚመጡ በሽታዎች፣ አደጋዎች እና ችግሮች ለመጠበቅ እንደሆነ ይታመናል። ይኸ ደግሞ የሰው፣ የእንስሳትና የምርት ጤናን በማረጋገጥ የማኅበረሰቡን ዘላቂነትና መረጋጋት ለማስጠበቅ ወሳኝ ነው። በተጨማሪም፣ የዚህ ሥርዓት መደበኛ አከባበር ከማኅበረሰቡ ባህላዊ የቀን መቁጠሪያ እና ዓመታዊ የእርሻ ዑደት ጋር ያለውን ግንኙነት ያሳያል።

በጥቅምት ወር የሚከበረው ሥርዓት የሚከናወነው ወሩ በገባ በአምስተኛው ቀን ነው። ይህ ቀን በጾም ላይ ከዋለ፣ ለሥርዓቱ የሚሆን የተለየ የፍስክ ቀን ይመርጣሉ። የፍስክ ቀን የሚመረጠው ደም ስለሚፈስ ነው። በብዙ ባህሎች ውስጥ ደም መፍሰስ መንጻትን እንደሚያመጣ ወይም የኃጢአትን ዋጋ እንደሚከፍል ይታመናል። በአካባቢው፣ “ክረምት በሐምሌ አቦ ተሹሞ በጥቅምት አቦ ይሻራል” የሚል እምነት አለ። ክረምቱ ከገባ በኋላ ከብቶች ከየቤታቸው ወጥተው በጋራ ወደ መስክ ይሰማራሉ። ለሦስት ወራት ያህል ከቆዩ በኋላ ክረምቱ እንደወጣ በዚህኛው ቀን ወደ ማደሪያቸው ይመለሳሉ። በዚህ በዓል ላይ ደም ይፈሳል፤ ድግስ ይደገሳል፣ ከብቶቹም ወደ በረታቸው እንዲገቡ ይደረጋል። በጥቅምት ወር ሲከበር፣ የአካባቢው አባቶች እንደሚመሰክሩት፣ "በክረምቱ ከተለያዩ አደጋዎች ተጠብቀን፤ እንኳን በሰላም ለዚህ ደረስን" የሚል የምስጋና መልእክት ለማቅረብ ነው።

በግንቦት ወር የሚከበረው የ"ግስ" ክበራ ሥርዓት የሚከበርበት ምክንያት ወሩ በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘር የሚዘራበትና የክረምት መግቢያ ወቅት በመሆኑ ነው፡፡ በቀዬው የሚገኘው ሁሉ (ሰው፣ ሰብሉና እንሰሳቱ) ከክረምቱ ጋር ተያይዞ ከሚከሰት ችግር እንዲጠበቅ፣ የሚዘራውን እህል ምድሯ እድትቀበለው፣ ወቅቱ ለዘር እንዲሆን ለመማጸን፣ ክረምቱን ተከትሎ የሚመጡ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ችግሮች እንዳይከሰቱ ቀድሞ ለመከላከል በማሰብ ነው፡፡
የ"ግስ" ሥርዓት የሚከወነው ሰዎች መሰባሰብ የሚችሉበት ቅርብ ከሆነ ቦታ ላይ ነው፡፡በክዋኔው ላይ የሚሳተፉትም የእድር አባላት ናቸው፡፡ Brown (2013) በማኅበራዊ ተቋማት ውስጥ ያሉ ማኅበራዊ ስርዓቶች የቡድኑን የጋራ ስምምነትና ተጠቃሚነት ያሳያል ይላሉ፡፡ ከዚህ አንጻር በተጠኚው ማኅበረሰብ በእድር አባላት መካከል የሚከወነው የ"ግስ" ክዋኔ ቂምና ጥላቻን ለማስወገድ፤ እርቅን ለማስፈንና በማኅበረሰቡ ዘንድ አብሮነትን ለመገንባት እንደሚያስችል መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህ ሥርዓት ውስጥ የሚከናወኑት ከበራዎች፣ በማኅበራዊ እሴቶች የሚመሩ ሲሆን፣ የ"በረት አባት" በሚባል የሥርዓት ራስ አማካይነት ይመራል። የበረት አባት ለሥርዓቱ የሚያስፈልጉ መዋጮዎችን የሚቆጣጠር፣ ቅራተኛው ሲያጠፋ የሚቀጣ፣ የዓመቱን ሥርዓት የሚያስከብር፣ ለእርድ የሚቀርበውን በግ ወይም ፍዬል የሚባርክ እና የዓመቱን ግስ ስርዓት የማስከበር ኃላፊነት የሚወስድ ግለሰብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሥርዓቱ የጋራ እሴቶችን፣ የቡድን ደንቦችን እና ሥነ-ምግባርን ለማስጠበቅ የሚረዳ የማኅበራዊ ቁጥጥር ዘዴ መሆኑን ያሳያል።

Sato (2011) በመዋቅራዊ ሥርዓት ውስጥ ቡድኖቹ የእርስ በእርስ ትስስር እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ደንቦች የቡድኖችን አንድነት ከማጠናከር ባሻገር የወል እሴቶቹ እንዲጠበቁ አስተዋጾ እንደሚኖረው ገልጸዋል፡፡ የግስ ሥርዓት የማኅበረሰቡን አብሮነት፣ ስነ-ምግባር እና በሕይወት የመኖር ችሎታ የሚያንጸባርቅ ወሳኝ የባህል ገፅታ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ሥርዓቱ የጋራ እሴትን፣ አመለካከትን እና ግቦችን በማጎልበት የማኅበረሰቡን መረጋጋት ለማስጠበቅ ያገለግላል። በአጭሩ፣ የ"ግስ" ሥርዓት ከኃይማኖታዊና ባሕላዊ ሥርዓት ባሻገር፣ የማኅበረሰቡን መዋቅራዊ ጤንነት የሚገነባና የሚያጠነክር ተቋም ነው።

በመሆኑም፣ የበረት አባት ማኅበረሰቡ በሚተዳደርበት የጋራ ደንብ መሠረት በእድር ተመርጦ ኃላፊነት ይሰጠዋል። ሲመረጥ በመስፈርትነት የሚያገለግሉት ሀብት፣ የአመራር ብቃት እና

ግብረገብነት ዋና መመዘኛዎች ናቸው፡፡ የተሻለ የከብት አመል ያውቃል በሚል እምነት፣ ቤተሰብ የማስተዳደር አቅም ያለው/በኢኮኖሚ የተሻለ፣ በእድሜ የበሰለ እንዲሁም በግስ ሥርዓቱ ለሚከበረው ሥርዓት ከሌሎች ተሳታፊዎች በተለየ ብዙ ድግስ በማውጣት ከበራውን የማስኬድ አቅም አለው ተብሎ የሚታመንበት መሆን አለበት። ከዚህ የተነሳ የ “ግስ” ክዋኔ ሥርዓቱን ለማስፈጸም የበረት አባት ትልቅ ድርሻ አለው።

ሥርዓቱ የሚከወነው ቅራት ባለበት፣ ሰዎችንና ከብቶችን ለማሰባሰብ በሚመችና ዛፍ ባለበት ቦታ ነው። ዛፍ ያለበት ቦታ የተመረጠበት ምክንያት በግሱ ክዋኔ ወቅት ለዕርድ የሚቀርበው የእንስሳ ደም ከዛፉ ሥር ያለች መንፈስ ከደሙ ትቋደሳለች በሚል እምነት ነው። በከበራ ሥርዓቱ ጠባቂ እንደሆነች የሚታመንባት የአዋይት መንፈስ የሚሰባሰቡ ሰዎችን ከተለያዩ አላስፈላጊ ክስተቶች ስለምትጠብቅ፣ ከሚቀርቡ ምግቦችና መጠጦች ቀድመው ያቀምሷታል። ለሥርዓቱ የሚያስፈልጉ ምግቦችና መጠጦች ጠላ፣ እንጀራ፣ አረቂ፣ ቡና፣ ንፍሮ ሲሆኑ፣ ለእርድ የሚቀርበው ደግሞ በግ ወይም ፍየል ነው።

እነዚህ ለግስ ሥርዓቱ የሚያስፈልጉ የምግብና የመጠጥ መዋጮዎች ከእድርተኞች ወይም በግሱ ሥርዓት ከሚሰባሰቡ ሰዎች በመዋጮ ይሰበሰባሉ። እንጀራ በቁጥር ተወስኖ እንዲሁም ጠላ በማንቆርቆሪያ እየተሰፈረ እኩል በማዋጣት ከበራው ከሚከወንበት ቦታ ይወሰዳሉ። በቦታው የሚወሰዱት የስለትና የመጠጥ ዓይነቶች በአብዛኛው የአልኮል መጠጦች ሲሆኑ፣ ከጠላ በመቀጠል አረቂ ለአዋይት ቆሌ ተገቢና የምትወደው መጠጥ እንደሆነ ይታመናል። ይሁን እንጂ የበረት አባት ከሌሎች ሰዎች በተለየ መልኩ ለእርድ የሚቀርበውን በግ በማቅረብ፣ አንድ እንስራ ጠላ እንዲሁም እያንዳንዱ ሰው ከሚያዋጣው እንጀራ በሦስት እጥፍ አስበልጦ በማዋጣት በግስ ሥርዓቱ በሚከበርበት ቦታ በመውሰድ የማስተናገድ ኃላፊነቱን ያከናውናል።

የ “ግስ” ሥርዓቱ በአብዛኛው እሁድና ቅዳሜ ቀን የሚከወን ሲሆን፣ የጾም ቀናት እና የሥራ ቀናት ለሥርዓቱ ማስፈጸሚያነት ተመራጭ አይደሉም። ምክንያቱም፣ በግስ ሥርዓት ላይ እርድ ስለሚፈጸም ተሳታፊዎቹ በጾም ቀን መመገብ ሃይማኖታዊ ሕጋቸው ስለማይፈቅድላቸው ነው። በመሆኑም፣ ከቀናት ረቡዕና ዓርብ አይመረጡም። ሥርዓቱን በጋራ ለማክበር ሰዎች ትኩረታቸውን ወደ ሌሎች ሥራዎቻቸው እንዳያዞሩና በተረጋጋ መንፈስ ለማክበር

እንዲረዳቸው በማሰብ የበዓል ቀናት ይመረጣሉ። በመሆኑም እሁድና ቅዳሜ ለዚህ ክዋኔ ተመራጭ ቀናት ተደርገው ይታሰባሉ።

በመሆኑም ለግስ ሥርዓቱ ያሰባሰቡትን ጠላ ከሽክላ በተሰራ እንስራ ሞልተው፣ እንጀራውንም አሰባስበው ከብቶች ከሚሰባሰቡበት ቅራት ዳር ከሚገኝ ዛፍ ስር በማስቀመጥ ይጠባበቃሉ፡፡ በዛፉ አካባቢ ለሰዎች መቀመጫ የሚሆኑ ወንበሮችና የበግ አጎዛዎች ያዘጋጃሉ፡፡ ሽማግሌዎች በተዘጋጁ በተቃቃ የበግ ቆዳ (አጎዛ)፤ ወጣቶች ደግሞ በወንበር ላይ እንደየዕድሜ ደረጃቸው ይቀመጣሉ፤ ቡና ይፈላል፤ አረቂ፣ በቂቤና በድቁስ የተዘጋጀ ቂጣ ይቀርባል (ምልከታ ግንቦት 9፣ 2017)፡፡

የበረት አባት በሚል ስም የተሾመው ሰው ለሥርዓቱ ያቀረበውን ምግብና መጠጥ ሰዎች ከመቅመሳቸው በፊት አዋይት ቆሌ እንድትቀምሰው ከእንጀራውም ሆነ ከመጠጡ ለማቅመስ በሚል ቆራርሰው በአራቱም አቅጣጫ ይበትናሉ፡፡ ምክንያቱም፣ አዋይት ቆሌ ሳትቀምሰው ሰው ከቀመሰው ክብር አለመስጠት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ለአዋይቷ ከአቀመሱ በኋላ የበረት አባቱን ጨምሮ በዕድሜ ታላቅ የሆኑ ሰዎች ከዚያም ወጣቶችና ህጻናት ይቀምሳሉ፡፡ ይህ ከታላቅ ወደ ታናሽ የሚቀርብ በመሆኑ በማኅበራዊ ደረጃው ታላቅን የማክበር እሴትን ያጠናክራል፡፡ በግስ ሥርዓቱ የሚፈጸሙ ተግባራት ከማኅበረሰቡ እሴት ጋር የተሳሰሩ ናቸው፡፡ ይህንን ሃሳብ Douglas (2003) ፊውስ የሚያስገኙ ከበራዊ ክዋኔዎች ጤንነትን ለማስጠበቅ ከመከወናቸው ባለፈ ከማኅበራዊ ስርዓትና የማኅበረሰብ መገለጫ እሴቶች ጋር የተቆራኙ መሆናቸውን የገለጹትን ሃሳብ ያሳያል፡፡

በግሱ ክዋኔ የተሰባሰቡ ሰዎች እርዱ እስኪፈጸም ከሚፈላው ቡና እየጠጡ ይቆያሉ፡፡ የአቦሉ ቡና ከተጠጣ በኋላ ሁለተኛው ቡና እየተፈላ ለእርድ የቀረበው በግ ይታረዳል፡፡ ‹‹…ቅራተኛው[4] ከብቱን ሰብስቦ አንድ ቅራት ላይ ያደርጋል፡፡ ርኩስ መንፈስ ሁሉ እንዲወገድ የሚሰዋው የበግ ደም ትልቅ ሚና እንዳለው ስለሚታመን እርዱ ቅራቱ ላይ ይደረጋል›› (ልምጭም ሚያዚያ 28፣ 2017 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)

ታርዶ የሚቀርበው የደም መስዋዕት የበግ ሆኖ ጥቁር ቀለም ካላቸው በስተቀር የቀይ፣ የነጭ፣ የዥንጉርጉር መሆን እንዳለባቸው ያምናሉ፡፡ ምክንያቱም ጥቁር የሠይጣን ምሳሌ ነው፤ አዋይ አድባር

[4] ቅራተኛ፡ ጠባቂ ሰው

አትቀበለውም የሚል እምነት ስላላቸው ነው[5]፡፡ በተጨማሪም የሚታረደው በግ ጸጉሩ ያልከረከረ፣ ጥፍሩ ያልዘረዘረ፣ ቀንዱ ያልጠረና ለጋ የሆነ መሆን አለበት፡ ምክንያቱም ለመስዋዕት ታዛዥ መሆን ስላለበት ነው፡፡ ይኸ ካልተተገበረ በጠባቂ መንፈስ ዘንድ ተቀባይነት አያገኝም፤ የሚቀርበው መስዋዕት አይደርስም፡፡ በተለይ በሴት ጾታ የምትጠራው አዋይት ጥበቃዋ ይቋረጣል ተብሎም ይታመናል፡፡

በመቀጠልም የሚታረደው መስዋዕት በተመረጠው ሰው ይባረካል፡፡ ‹‹በእርድ ሥርዓቱ የሚታረደውን እንሰሳ ለመባረክ የሚመረጠው ግሱ ሥርዓት ላይ ብዙ ድግስ በማውጣት ሰዎችን የማስተናገድ ኃላፊነት የተሰጠው የበረት አባት ወይም ባላባት የሆነ ሰው ነው›› (ደን መጋቢት 23፣ 2017 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) በማለት ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ለመስዋዕቱ ንጽሕና በማሰብ አራጅ ተመራጭ ይደረጋል፡፡

በግስ ሥርዓት የሚታረደው የበግ ደም ርኩስ መንፈስ በደሙ እንዲወገድና ስለርኩሰቱ የሚቀምሰው ካሳ ተደርጎ የሚሰጠው ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሰዎችንና እንስሳትን ጤናቸውን የሚያውክ ርኩሰት ከሚፈስለት ደም እንዲቀምስና በዚያ ደም የተሰባሰበው እንሰሳትና ሰዎች እንዲነጹ ይደረጋል፡፡ ለመስዋዕት የሚቀርበውን በግ የሚባርከው ሰው እርዱን በሚፈጽምበት ወቅት በግራና በቀኝ እጁ ሁለት ብርጭቆ ውሃ ይይዛል፡፡ ከባረከው መስዋዕት በግ ላይ በግራውና በቀኙ ከያዘው ውሃ የቸር ደም አድርገው ብሎ ሦስት ጊዜ ይደፋል፡፡ ይህም ደሙ በግራም በቀኝም ያለውን ሁሉ ጠብቅልን የሚል ትርጉም አለው፡፡

ከተባረከው ደም ላይ የደፋለትን የተረፈውን ውሃ አራጁ ከቀመሰ በኋላ እስካለቀበት ድረስ እየተቀባበሉ ይጠጡታል፤ ምክንያቱም በረከት ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡[6]

በታረደው የመስዋዕት ደም ከዛፉ አካባቢ ትኖራለች ተብላ ለሚታመንባት አዋይት ከተቋደሰች በኋላ ለእንሰሳቱ የሚረጨውን ደም የበረት አባቱ በዕቃ ይይዘውና አንድ ጊዜ ወይም ሦስት ጊዜ በመዞር በቅራቱ የተሰበሰበውን እንሰሳት በሙሉ በአባሎ ቅጠል ወይም በጭራ ይረጨዋል፡፡ ሦስት ጊዜ የሚዞርበት ምክንያት የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የሚገልጽ ሲሆን፣ አንድነቱ በቀዬው የሚገኘው ሁሉ

---

[6] ኮርክ ሚያዝያ 23፣ በቃለመጠይቅ

በአንድነት የሚጠበቅበትን የሚያሳይ ሲሆን ሦስትነቱ ደግሞ ሰዎችን፣ እንስሳትንና በቀዬው የሚገኘውን ሰብል የሚያሳይ ነው፡፡

ለመስዋዕት የፈሰሰው ደም በአባሎ ቅጠል ወይም በጭራ የሚረጨበት ምክንያት ሁሉንም የተሰባሰቡትን እንሰሳት ከደሙ እንዲያዳርስላቸው ለማድረግ ነው፡፡ በሌላ መንገድ ደግሞ ከሌሎች እጽዋት በተለዬ አባሎ ቅጠል የተመረጠበት ምክንያት አባሎ በደጋማው አካባቢ በተለይ የዕቃ ማጠኛና ጥሩ ሽታ ያለው በመሆኑ በውቂያ ወቅትም እንስሳትን ለመመረቂያ ያገለግላል፤ በግስ ወቅትም ለማንጻት ተግባር ይጠቅማል፡፡ ‹‹በአባሎ ቅጠል መፀዳዳት ርኩሰት ነው፤ ሰዎች በሌላ እጽዋት ሊጠቀሙ ቢችሉም በአባሎ ግን……፡፡›› (ደን ሚያዝያ 28፣ 2017 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ) በማለት ለእጽዋቱ ያላቸውን የማንጻት ሚና የሚያስረዳ ሃሳባቸውን ይገልጻሉ፡፡

በተጨማሪም ደሙን በ ‹‹ጭራ›› የሚረጨበት ምክንያት የቆሻሻው፣ የዝንቡ ሁሉ ማባረሪያና መከላከያ በመሆኑ በግሱ ሥርዓትም የማይፈለገው ነገር ሁሉ እንዲወገድ በሚል እምነት ጭራ ከሌላው ነገር ሁሉ በተለዬ ተመራጭ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ እያንዳንዱ ተግባራት ንጽሕናን በማያሳጡ ነገሮች የመፈጸም ተግባር ለሚፈሰው ደም ያላቸውን ክብር የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም የከብቶችን ጤንነት ደም በመርጨት እንደሚጠብቁ ሲታመን ሰዎች ደግሞ ከታረደው በግ[7] ስጋውን በመብላትና በመታደም እንደነጹ ይታሰባል፡፡

ይህም በማኅበረሰቡ ዘንድ እንሰሳቱን ከሚያጠቃ በሽታ፣ በሰውና በቀዬው ጉዳት ከሚያስከትል ክስተት ሁሉ ያነጻል ተብሎ የሚታመንበት ሥርዓት በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም የግስ ሥርዓትን በቡድን ተሰባስቦ የማክበር ልማዱ በቡድኑ ውስጥ ሰዎች ያላቸውን የአብሮነት ማኅበራዊ እሴት ለማስጠበቅ እና ከበሽታ ለመፈወስ የሚጠቀሙበት በመሆኑ ግለሰቦችን ከቡድኑ ከሚነጥል ርኩሰት ለማንጻትና ቡድናዊ አደጋን ለመከላከል የሚረዳ አምልኳዊ ሥርዓት መሆኑ ይታመንበታል፡፡

## በግስ ሥርዓት ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ ደንቦች

Gray et al. (2022) "የመንጻት መመሪያዎች በባህላዊ ሥርዓቱ ውስጥ የተለዩ የትክክልና ስህተት እሳቤዎች አሏቸው፡፡ ስለሆነም እነዚያን የንጽሕና ደንቦች መጣስ የቡድኑን አባላት ታማኒነትና ባህርያት ጠቋሚዎች ናቸው" ይላሉ፡፡ በመሆኑም፣ በግስ ሥርዓት አተገባበር ሂደትም ሰዎች በሥርዓቱ ለመሳተፍ የሚጠበቅባቸውን

[7] በቆላማው አካባቢ ፍየል፣ በደጋማው በግ ይታረዳል፡፡

ደንብ ማሟላት እንደሚገባ የሚታመን ሲሆን፣ የሥርዓቱ አካል ማድረጊያ መንገዶችን አለማክበር ደግሞ ርኩሰት እንደመፈጸም ይቆጠራል፡፡

"የግስ ስርዓት" የተረጋጋ ማኅበራዊ ስርአት ለመፍጠር የሚያስችል የተደራጀ መዋቅር አለው። "የበረት አባት" የስርአቱ ማዕከላዊ አካል ሲሆን፣ ቁልፍ የቁጥጥር፣ የጥበቃ እና የቅጣት ተግባራትን ያከናውናል። የግጦሽ ቦታዎችን ከማስከለል፣ የከብት ስርቆትን ከመከላከል እና ለተጎዱ ሰዎች ካሳ ከማስከፈል አንስቶ፣ ደንቦችን ለማይተገብሩ ተሳታፊዎች ቅጣቶችን እስከመወሰን ድረስ የበረት አባት ሚና ወሳኝ ነው። ተሳታፊዎች ወይም እድርተኞች ደግሞ የስርአቱን ቀጥተኛ የክዋኔ ደንቦች በማክበር እና "ጥሩ ስነምግባር" በማሳየት የራሳቸውን ተግባር ይወጣሉ። የቅጣት ደንቦች በበረት አባት የሚወሰኑ ቢሆንም፣ "በእድርተኞቹም ዘንድ ስምምነት የተደረገበት" መሆኑ የስርአቱን የጋራ ተቀባይነት እና መረጋጋት ያጠናክራል። ይህ ሁሉ የስርአቱን መረጋጋት የሚያረጋግጡ ሲሆን፣ Avichal (2023) እንዳብራሩት ባህላዊ ስነምግባር ግለሰባዊ ባህሪን በመቅረጽ ለስርአቱ መዋቅር ወሳኝ ድርሻ አለው።

"ንጹህነት" የስርዓቱን ህጎች፣ ደንቦች እና "ጥሩ ስነምግባር" የሚያከብሩ ግለሰቦችን ይወክላል። እነዚህ ግለሰቦች የጋራ ጥቅም ጠባቂዎች በመሆን የህብረተሰቡ የተከበሩ አባላት ናቸው። በሌላ በኩል፣ "ርኩሰት" የሚያመጡ ድርጊቶች እና ግለሰቦች አሉ። ለምሳሌ፣ የጠባቂው ጥፋት የተነሳ እንስሳ ቢጠፋበት ወይም ለስርዓቱ የሚደረገው መዋጮ ካልተሰበሰበ እንደ "ምግባራዊ ስህተት" ይታያል። ከሁሉ በላይ ደግሞ፣ "የከብት ስርቆት" እንደ ከባድ ርኩሰት የሚቆጠር ሲሆን፣ ይህን የሚያደርጉ ግለሰቦች "ከቡድናዊ እሴቱ ይገለላሉ"። ይህ መገለል የስርዓቱን ንጽህና ለመጠበቅ እና ከሚያስጋ ርኩሰት ለመጠበቅ የሚወሰድ እርምጃ ነው። ስርዓቱ ርኩሰትን ለማስወገድ "የመንጻት ሥርዓት" ይጠቀማል፣ ዋናውም "በበረት አባት" የሚፈጸሙ የቅጣት ደንቦች ናቸው። የቅጣቱ ዓላማ ግለሰቡን ከቡድኑ ለዘላለም ማግለል ሳይሆን፣ ድርጊቱን በመቅጣት እና "በይቅርታ ተመልሶ አብሮ እንዲያከብር" በማድረግ ወደ ስርዓቱ ንጽህና እንዲመለስ ማስቻል ነው። ይህ ሂደት የስርዓቱን የጋራ መተባበር እና የመተዛዘን እሴቶችን የሚያጠናክር ነው።

Avichal (2023) በባህል ውስጥ ያሉ ስነምግባራዊ እሴቶች የግለሰቦችን ባህሪ ለመቅረጽ ምቹ ሁኔታዎችን እንደሚፈጥሩ ገልጸዋል፡፡ በግስ ሥርዓቱ የበረት አባት የግጦሽ ቦታዎችን የማስከለል፣ የከብት ስርቆት እንዳይፈፀም ጥበቃን ማጠናከር፣

በከብቶች የተበላን አዝመራ ለተጎዳበት ሰው ካሳ የማስከፈል ተግባራትን ይፈፅማል፡፡ ከዚህ አንጻር በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ በአብዛኛው የከብት ስርቆት ስለሚከሰት ይህንን ተግባር የሚፈጽሙ ግለሰቦች ከቡድናዊ እሴቱ ይገለላሉ፡፡ ግለሰቡ ባጠፋው ከባድ ጥፋት ምክንያት ለቡድኑ አስጊ ችግር የሚፈጥር ከሆነ ደግሞ የበረት አባቱ የቅጣቱን ህግ ይፈጽምና ያጠፋው ሰው በይቅርታ ተመልሶ አብሮ እንዲያከብር ያደርጋል፡፡

Cossu (2024) ሥነ-ምግባራዊ ንጽሕና በስነሰብ መስክ የማኅበረሰብን የሞራል ሥርዓት የሚጠብቁ ደንቦችን በማክበር የሚገለጥ ሲሆን፤ ደንቦችን አለመጠበቅ ደግሞ ከሥነ ምግባራዊ ርኩሰት ጋር እንደሚዛመድ ይገልጻሉ። ከዚህ አንጻር በግስ ሥርዓት መልካም ሥነምግባር የማኅበረሰቡን ጥሩ የሰዋዊነት መገለጫ ተግባራት በመፈጸም ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር ስምምነት ኑሮት በሰላም ሕይወቱን የሚመራ ሰው መሆን እንደሚገባ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡ ‹‹ከሀገር ገንዘብ የበሉ ወይም በሀሰት ገንዘብ ወስደው ያልመለሱ እኛ ጋር ሊያከብሩ አይችሉም፡፡ ከሠው ጋር በተለያዩ ምክንያት ተጣልተው ያልታረቁ፣ ቂመኞች ከሰዎች ጋር መስማማት የማይፈልጉትን በበዓሉ ዕለት እንዴት አብረው ይሰባሰባሉ? በዓሉን ለማክበር ከሰው ጋር የሚግባባ ባህሪ ሊኖር ይገባል፤ አለዚያ ሰው ያርቃቸዋል›› (ልምጭም ግንቦት 5፣ 2017 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ስለሆነም፣ በግስ ሥርዓቱ የሚሳተፉ ግለሰቦች ጥላቻ ያለባቸው ከሆነ ቀድመው እርቅ መፈጸም ይኖርባቸዋል፡፡

ይህንን ያልተገበረ ሰው የሚሳተፍ ከሆነ የማኅበረሰቡን የአብሮነት ደንብ እንደመጣስ ይቆጠራል፡፡ ምክንያቱም ለመስዋዕት የቀረበው ደም ፍቅርን፣ እርስ በእርስ መከባበርን ታማኝነትን የሚፈልግ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ‹‹የተጣሉ ሰዎች ካሉ ለደሙ ሲባል ለዚያለትም እንኳ ቢሆን እንዲታረቁ ይደረጋል›› (ደን ሚያዝያ 28፣ 2017 በቃለመጠይቅ)፡፡በመሆኑም፣ በሰዎች ላይ ቂምና ጥላቻ ያለባቸው፣ የሰረቁ፣ ግድያ የፈጸሙ ግለሰቦች ከማኅበረሰቡ የተከለከለ ደንብ ያፈነገጡ መሆናቸው ስለሚታሰብ እነዚህን የማይፈቀዱ ተግባራትን ግሱ ከመተግበሩ በፊት ያስተካክላሉ፡፡ ይኸንን የማስተካከል ተግባር የሚፈጽመው በዋናነት የበረት አባቱ በእድር በማመልከት የደንብ ጥሰት እንዳይኖር የሰዎችን የተዛባ ተግባር ወደነበሩበት የመመለስ ሥራ ይሰራል፡፡ ታላቁን የሰደበ ራሱን ዝቅ አድርጎ ይቅርታ ያቀርባል፤ የሰረቀ ይመከርና ለሰረቀው ግለሰብ ካሳ ይሰጣል፡፡ ግድያ የፈጸሙ ግለሰቦች ደግሞ ከተበዳይ ወገን ጋር በደምና ቃለመሃላ እንዲታረቁ ይደረጋል፡፡በመሆኑም፣ ሥርዓቱ

ማኅበረሰባዊ ትስስርንና ስርዓትን ለማስፈን ያለውን ውስብስብና ውጤታማ ዘዴ ያሳያል።

ከዚህ የባህርይ ርኩሰት ያልነጹ ሰዎች ፈውስ ለሚገኝበት የግስ ሥርዓትና ለሚፈሰው ደም አክብሮት እንደሌላቸው ይታሰባል፡፡ በሌላ መንገድ ደግሞ በጥላቻ ውስጥ ሆኖ አብሮ መብላትና መጠጣት የማኅበረሰቡ እሴት አይደለም፡፡[8] ይኽ ደንብ ቡድናዊ ፈውስን ከማስገኘቱ ባለፈ አብሮነትን የማጠናከር ፋይዳ እንዳለው ያስረዳል፡፡ ስርዓቱ በተለየ ሁኔታ የሰዎችን ባህርይ ለማስተካከል የሚያስችሉ መዋቅራዊ ተግባራትን ያካትታል። "የበረት አባት" እንደ ማዕከላዊ ተቋማዊ አካል ሆኖ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ "ቂምና ጥላቻ ያለባቸው፣ የሰረቁ፣ ግድያ የፈጸሙ" ግለሰቦችን "የተዛባ ተግባር ወደነበሩበት የመመለስ" ስራ ይሰራል፤ ይኸም የስርዓቱን መረጋጋት እና ቀጣይነት የሚያረጋግጥ ቁልፍ ተግባር ነው።

ይኸ የማስተካከል ሂደት ግለሰቦችን ከማግለል ይልቅ የሥርዓቱ አካል አድርጎ ለማቆየት ያለመ ሲሆን፣ የቡድኑን መዋቅር ለጠናክራል ያገለግላል። ለምሳሌ፣ ታላቁን የሰደበ ይቅርታ እንዲጠይቅ፣ የሰረቀ ካሳ እንዲከፍል፣ እና ግድያ የፈጸሙ ደግሞ "በደምና ቃለመሃላ እንዲታረቁ" መደረጉ፣ የእያንዳንዱን ስህተት በማረም ማኅበራዊ ስርዓቱን እንደገና የማስፈን ተግባርን ይወክላል። እነዚህ የይቅርታና የማስታረቅ ስርአቶች የግለሰቦችን ተግባር ከመቅረጽ ባለፈ፣ የማኅበረሰቡን ስምምነትና አብሮነት ያሳድጋሉ።

"የማስተካከል ተግባር" እና የሚፈጸሙት ቅጣቶች–እንደ ይቅርታ መጠየቅ፣ ካሳ መክፈል፣ ወይም በደምና ቃለመሃላ መታረቅ–ርኩሰትን ለማስወገድ እና ግለሰቦችን ወደ ንጹህነት ለመመለስ የሚያገለግሉ የመንጻት ሥርዓቶች መተግበሪያ ነው። "በጥላቻ ውስጥ ሆኖ አብሮ መብላትና መጠጣት የማኅበረሰቡ እሴት አይደለም" የሚለው ደግሞ ርኩስ የሆነ መንፈስ ያላቸው ሰዎች የጋራ ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች አካል ሊሆኑ እንደማይችሉ ያመለክታል። እነዚህ የመንጻት ሂደቶች የቡድንን ንጽህና ከመጠበቅ ባሻገር፣ "ቡድናዊ ፈውስን" በማስገኘት እና "አብሮነትን በማጠናከር" ማኅበረሰቡን ወደ ንጹህና የተቀራረበ ህብረት ይመልሰዋል።

የግስ ስርዓት የማኅበረሰቡን መረጋጋት እና ቀጣይነት የሚያረጋግጥ ወሳኝ የማኅበራዊ መዋቅር ነው። ይህ ስርዓት የአመራር ምርጫን፣ የኃላፊነት ቅብብሎሽን እና ሌሎች ቁልፍ ማኅበራዊ ተግባራትን በማከናወን የህብረተሰቡን ህልውና ያጠናክራል።

[8] ደን ግንቦት 5፣ 2017 በቃለመጠይቅ

የግስ ስርዓት የማኅበራዊ መረጋጋት ዋና መሠረት አስተማማኝ አመራር ነው። ስርዓቱ ግልጽ በሆኑ ደንቦች የሚመራ በመሆኑ፣ የመሪዎች ምርጫ ያለ ጥርጥር እና በመልካም ስነምግባር ላይ ተመስርቶ ይከናወናል። ይህ ሂደት ግጭትን የሚቀንስ ሲሆን፣ በህብረተሰቡ አባላት መካከል መተማመንን ይፈጥራል። በተጨማሪም፣ ኃላፊነትን ከበረት አባት ወደ ተተኪው የሚያስተላልፈው የ"ጽዋ ወይም ብርጭቆ ጠላ" ሥርዓት **ፍቅርንና የኃላፊነት ተቀባይነትን** በምሳሌያዊ መንገድ ያሳያል። ይህ የአምልኮ ሥርዓት አመራርን ከማስተላለፍ ባለፈ ማህበራዊ ትስስርን እና መከባበርን ያጠናክራል።
የግስ ሥርዓት ተግባራት በምርቃት ሲጠናቀቁ ማኅበረሰቡ የጋራ ስኬትን እና መልካም ምኞትን ያከብራል። ከምርቃት በኋላ የሚደረገው የስለት መሳል ሥርዓት **መንፈሳዊ ንጽህናን** እና ግለሰቦች ከማኅበራዊ እሴቶች ጋር ያላቸውን ቁርኝት ያሳያል። ስለት መሳል ማለት አንድ ግለሰብ ከተወሰነ ፍላጎት ለመውጣት ወይም የተሻለ ሁኔታ ለማግኘት **ቃል የሚገባበት** ወይም **ተስፋውን የሚያሳይበት** መንገድ ነው። ይህ ተግባር የግለሰቦችን ስሜታዊና መንፈሳዊ ደህንነት በማጠናከር **ማኅበራዊ ውህደትን** ያጎላል። በአጠቃላይ፣ የግስ ሥርዓት በውስጡ ያሉት የተለያዩ ክፍሎች አንድ ላይ በመስራት የአመራርን ቀጣይነት፣ የባህል እሴቶችን እና ማኅበራዊ ስምምነትን ለማስጠበቅ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ።

የበረት አባቱ የሚሳሉ ሰዎችን ስምና የስለት ዓይነት ይመዘግባል፡፡ በቀጣይ ዓመት የተሳሉትን ማቅረብ ከጠባቂ መንፈስ ጋር ቃል እንደመግባት ይቆጠራል፡፡ ‹‹የሚገርምሽ ነገር ተመርቄ ሥራ አጣሁ፤ ከዚያ የእኛ የግስ ከበራ እለት ሥራ ካገኘሁ አንድ ጅን አረቂ አቀርባለሁ ብዬ ተስዬ ወዲያውኑ መሥሪያ ቤት ተቀጠርኩ›› (የጁቤ 01 ቀበሌ፤ ግንቦት 5፣ 2017 በቃለመጠይቅ) ይላሉ፡፡ በግስ ሥርዓት ስለት ተስለው የተሳካላቸው ሰዎች ቃላቸውን ጠብቀው ማቅረብ የሥርዓቱን ደንብ እንደማክበር ይቆጠራል፡፡[9]

ስርዓቱ ማኅበረሰቡን በሚያደራጅበት መንገድ ግልጽ የሆኑ የመግቢያ መስፈርቶች አሉት። በሌላ መንገድ በግስ ሥርዓት ለመሳተፍ ከሚያስፈልጉ ደንቦች መካከል እድርተኛ መሆን ዋናው ነው፡፡ እያንዳንዱ ጭሰኛ[10] በግስ ሥርዓት ለመሳተፍ የግድ በእድር ውስጥ መካተት እንደሚገባው መረጃ ሰጪዎች ያስረዳሉ፡ ‹‹እድር ውስጥ የተካተተ ሰው…ግስ በሚከበርበት ቀን የሚዋጣውን ምግብና

[9] ልምጭም ሚያዝያ 28፣ 2017 በቃለመጠይቅ

[10] ትዳር መስርቶ ጎጆ ቀልሶ የሚኖር

መጠጥ በማሰባሰብ ይዞ መቅረብ ይችላል፡፡...አድርተኛ ሆነሽ ነው መሳተፍ የምትችይ፤ እድር ያው በየጎጡ ስላለ በየእድራችን እናከብረዋለን›› (የጁቤ 01 ቀበሌ፣ ግንቦት 5፣ 2017 ከተካሄደ ቡድን ውይይት የተወሰደ)፡፡ ይህ ደግሞ ለግለሰቦች የስርዓቱ ተግባራዊ አካል ለመሆን ቅድመ ሁኔታ ነው።

ይሁንና በቀድሞው የግስ ሥርዓት የሰዎች ማንነት ባልታወቀበት፤ ቋሚ ነዋሪነታቸው ማረጋገጫ በሌለበት ሁኔታ መጤ ወይም እንግዳ የሆነ ሰው በግስ የመንጻት ሥርዓት ገብቶ እንዲሳተፍ አይፈቀድም ነበር፡፡ ‹‹መጤን እኛ እንግዲህ ተከርቸም እንለዋለን፤ ያው ተከርቸም በብዛት ከሌላ ቦታ ወደ እኛ መጥተው ያገቡ ወንዶችን ነው፤ ተከርቸም የሆኑ ሰዎች አሁን ላይ በእድር ውስጥ ገብተው አባል ከሆኑ አልፎ አልፎ ይሳተፋሉ›› (ደን መጋቢት 21፣ 2017 በተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ስለሆነም እንግዳ የሆኑ ሰዎች/መጤዎች በእድር ውስጥ ከተካተቱ የመሳተፍ ዕድል እንዳላቸው ይገልጻሉ፡፡ "የጋራ ለሚተዋወቁ፣ ቤተሰባዊ ለሆኑ፣ በማኅበረሰቡ ዘንድ ተወልደው ያደጉ ሰዎችን ትስስርና አብሮነት መጠበቂያ::

የእነሱ ማንነት እና ታሪክ ያልታወቀ በመሆኑ፣ "በሽታ ወይም ከሌላ አደጋ ለመጠበቅ" ሲባል በሚፈስ ደም ውስጥ መግባታቸው "የጤና ችግር ሊፈጥር ይችላል" የሚል ስጋት ስለነበር ነው። ስርዓቱ የራሱን ንጽህና እና የጋራ ደህንነት ለመጠበቅ ሲል ማን እንደ "ንጹህ" እና ማን እንደ "ርኩስ" እንደሚወሰድ የሚወስንበትን መንገድ ያንፀባርቃል።በመሆኑም፣ በቡድኑ ውስጥ ከበሽታ ወይም ከሌላ አደጋ ለመጠበቅ ተብሎ በሚፈስ ደም ዘው ብሎ መግባት የጤና ችግር ሊፈጥር ይችላል፤ ለሚቀላቀለውም ሰው ሆነ ደሙን በማፍሰስ ለመዳን የሚያምኑ ሰዎች የጤና ችግር ያስከትላል[11]፡፡ በመሆኑም በግስ ሥርዓት የሚፈሰው ደም በጋራ ለሚተዋወቁ፣ ቤተሰባዊ ለሆኑ፣ በማኅበረሰቡ ዘንድ ተወልደው ያደጉ ሰዎችን ትስስርና አብሮነት መጠበቂያ መሆኑ ስለሚታመን እንግዳ መሆኑ የታመነበትን ሰው አልፎ አልፎ ከማሳተፍ የሚከለክሉ ቢኖሩም በአሁኑ ጊዜ በእድር የተካተቱ ከሆነ ይሳተፋሉ፡፡

በሌላ መንገድ በአሁኑ ጊዜ ትኩረት የማይሰጠውና ለውጥ የተደረገበት ደንብ የዘር ንጽህና ነው፡፡ ቡዳነት፣ ፋቂነት፣ ሸማኔነት፣ ሸክላ ሰሪነት፣ ቀጥቃጭነት ግስ ሥርዓት ላይ አይሳተፉም ነበር፡፡ ‹‹...ባላባት መሆን ትልቅ ክብር አለው፤ ግስ ሥርዓቱ ላይ የሚያሰባስበንን በግ የሚያርደው ሰው ባላባት የሆነ ሰው ነው›› (ደን

[11] ደን መጋቢት 23፣ 2017 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ

መጋቢት 23፣ 2017 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ባላባት ያልሆኑ ሰዎች በማኅበረሰቡ ዘንድ በጋብቻ መስተጋብርም ሆነ በግስ ተሳትፎ የተከለከሉና ርኩስ መንፈስ አለባቸው ተብሎ ስለሚታሰብና አዋይ አድባር ትቆጣለች የሚል እምነት አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሥርዓቱን በእድር በመሰባሰብ ማክበር በመጀመሩ እና በእድር የተካተቱ ሰዎች ስለሚያከብሩት ለመስፈርቱ ብዙም ትኩረት እየተሰጠው አለመሆኑን መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ፡፡ አሁን ላይ "እንግዳ የሆኑ ሰዎች/መጤዎች በእድር ውስጥ ከተካተቱ የመሳተፍ ዕድል እንዳላቸው" መገለጹ፣ እድርተኛ መሆን እንደ መንፈሳዊ የመንጻት ሂደት ወይም ርኩሰትን የሚያስወግድ ዘዴ ሆኖ እንደሚያገለግል ያመለክታል።

በተጨማሪም፣ በግስ የአብሮነት በዓል ላይ የዛር መንፈስ ያለባቸው ወይም አጉሪዎች አይሳተፉም፡፡ “ባለዛር ተብለው የተለዩ ሰዎች ህመሙ በራሱ ከማኅበራዊ አብሮነት የሚነጥል መንፈስ መሆኑ በማኅበረሰቡ ዘንድ የታወቀ ስለሆነ አንድም በራሳቸው ምክንያት እንዳይሳተፉ መንፈሱ ይከለክላቸዋል፡፡ በሌላ መንገድ ደግሞ ግስ ላይ በሚሰባሰበው ሰው ዘንድ ተቀባይነት አይኖራቸውም” (ደን ግንቦት 5፣ 2017 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ በመሆኑም፣ ዛር በራሱ መንፈሱ ባደረበት ግለሰብ ላይ ሆኖ የሚፈልገው ነገር እንዲሟላለት የሚያስገድድ እና ከሰዎች ጋር መልካም ተግባቦትን የሚከለክል በመሆኑ ግስ ላይ የሚሳተፉ ሰዎች ከዚህ የጸዱ መሆን እንዳለባቸው ይታመናል፡፡ ‹‹..በግስ የሚሰባሰበው የጥርቅም ምግብ ስለሆነ ዛሩ ይህንን እንዳይበሉ ስለሚከለክል ከሌላው ሰው ጋር መግባባት አይችሉም፤ ዛር ያለበት ሰው የፍዬል ሥጋም አይበላም›› (ደን መጋቢት 22፣ 2017 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ በመሆኑም በባሶሊበን ማኅበረሰብ ዘንድ የዛር መንፈስ ያለባቸው ሰዎች ብቸኝነትን የሚፈልጉ እና ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖራቸውን መግባባት ስለሚረብሽ ለክበራው ታሳቢ አይደረጉም፡፡ በመሆኑም፣ ዛሩ ባይተዋርነትን አብዝቶ ስለሚወድ ተሳታፊዎቹ ከዚህ መንፈስ የተለዩ መሆን እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ፡፡

የቀረቡት ሃሳቦች እንደሚያሳዩት በግስ ሥርዓት ለመሳተፍ ለማኅበራዊ እሴት እና አብሮነት የሚረዱ ተግባራትን መፈጸም በማኅበራዊ እሴቱ ውስጥ ለሚተዳደሩ ግለሰቦችና ቡድኖች መመሪያ በመሆናቸው የሥርዓቱን ደንብ የማክበር ተገቢነትና ተገዢነት የንጽሕና መገለጫ መሆኑን ያሳያሉ፡፡ ይህንን እሳቤ Douglas (2003) መርከስ ካለ የሚጠበቅ ‹‹ሥርዓት›› አለ ይላሉ፡፡ ስለሆነም፣ የግስ ሥርዓት ደንብን መጠበቅ የንጽሕናን ተምሳሌታዊነት ይገልጻል፡፡

## የሚወገዱ የርኩሰት ክስተቶችና የሚያነጹ ተግባራት

የግስ ሥርዓት የሚከበረው ቡድናዊ አብሮነትን ከሚያናጉ የርኩሰት ክስተቶች ለማንጻት እንደሆነ ከላይ በቀረቡ መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ Blidstein (2017) እና Duschinsky et al. (2016) ርኩሰት የማጥቃት ሃይል ካላቸው ርኩስ መንፈሶች ጋር የሚገናኝና ከእነዚህ ክስተቶች በመንጻት ሥርዓትን ለመመለስ ከበራዊ የአምልኮ ስርዓቶች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ የተነሳ የግስ ሥርዓት የሚከወነው በቡድን በመሰባሰብ ቀዬውን ከተፈጥሮ አደጋ፣ እንሰሳቱንና ሰውን ከሚቀስፍ በሽታ እንዲሁም ሰብሉን ከሚያወድም ነፍሳት ለመጠበቅ እንደሆነ በማሰብ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር በግስ የአምልኮ ሥርዓት በመጠቀም ከሚወገዱ የርኩሰት ክስተቶች መካከል የሰዎችንና እንሰሳትን ጤና የሚያሳጣ ተላላፊ በሽታ አንዱ ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ ለማስረዳት፡- ‹‹ቸነፈር፣ ጉንፋን እና ተኸር ከገባ ሰውም በጉንፋኑና በቸነፈሩ መመታቱ ነው፤ በጉም ሆነ ሌላው እንስሳት በበሽታ ወረርሽኝ ወይም ተኸር[12] ማለቁ ነው፡፡ አንድ ቤት የሰውም ሆነ የእንሰሳት በሽታ መግባት ከጀመረ ሁሉንም ሰው ያዳርሰዋል፤..ይዛመታል፡፡ የግስ ደም ወረርሽኙን ያርቃል›› (የጁቤ 01 ቀበሌ፣ መጋቢት 23 ከተካሄደ የቡድን ውይይት) ይላሉ፡፡ በመሆኑም ግስ ሥርዓት ላይ የሚፈሰው ደም ተላላፊ በሽታን ያነጻል ተብሎ ይታመናል፡፡

በተጨማሪም፣ በግስ ሥርዓቱ የተረፈ ምግብና መጠጥ እንዲሁም የታረደውን የበግ ሥጋ ወደ ቤት መመለስና መጠቀም ርኩሰትን ይዞ ይመለሳል የሚል ዕምነት አላቸው፡፡ ስለሆነም፣ ከአንድ ቀን በላይ ለሚተርፍ ምግብና መጠጥ በድጋሜ መሰባሰብ የእድርተኞች ምርጫ ስለሆነ ተጨማሪ ሳያሰባስቡ በነበረው ትርፍ ድግስ እየተስተናገዱ የተዋጣው ድግስ እስከሚያልቅ ድረስ ይከበራል፡፡ ‹‹በዓሉ በሚከበርበት ቅራት የተሰበሰበው ነገር እዚያው ከቅራቱ ጨርሶ መምጣት አለዚያ ትርፉን መድፋት እንጂ ትርፉን መመለስ አይቻልም፡፡ የተወሰደ ነገር አይመለስም፤ ትርፉ በሽታ ይዞ ያመጣል፡፡›› (ደን ቀበሌ፣ መጋቢት 23፣ 2017 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ በመሆኑም በባሶሊበን የግስ ሥርዓት ላይ የሚተገበሩ ማስፈጸሚያ ሥርዓቶች ለርኩሰት ነገር ማራቂያ ስለሆኑ ትርፍ ነገር ከመመለስ ይልቅ በቦታው መጠቀም ተገቢ መሆኑ ይታመናል፡፡

በመሆኑም፣ እንሰሳቶቻቸውንም ሆነ ማኅበራዊ ጤናማነታቸውን ከሚበክል መንፈስ ለመንጻት ሲባል ማስጠበቂያ ስርዓት በመሆኑ

[12] ወረርሽኝ

በየዓመቱ ይተገብሩታል፡፡ ‹‹ግሱ መከበሩ ከተቋረጠ ጠባቂ ‹‹አዋይ አድባር››[13] ትቆጣና ሰውና እንሰሳቱ ሊሞት ይችላል፡፡ የደብሩ አዋይት እንዳትቆጣ ወቅቱን ጠብቀን እናከብራለን›› (የላምገንጅ መጋቢት 28፣ 2017 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ስለሆነም፤ የግስ ሥርዓት ለመስዋዕት[14] የሚቀርበው ደም ካልፈሰሰና ሌሎች ሥርዓቶች ካልተተገበሩ የጠባቂ መንፈስ ቁጣ ይደርስብናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከዚህ የተነሳ የተለመደውን ሥርዓት በመሰባሰብ ማክበር ንጽሕናን እንደማስጠበቅ ይቆጠራል፡፡

ሌላኛው በግስ ሥርዓት የሚነጻው የ"በረድ" ተፈጥሯዊ አደጋ ነው፡፡ የበረድ አደጋ የሚከሰተው በማኅበረሰቡ የታወጁ የበረድ ቀናትን የማክበር እሴት ሲጣስ መሆኑ ይታመናል፡፡ "...የበረድ በዓላት ተብለው የተለዩ ቀናት አሉ፤ መስከረም አስር ቀን እና የበዓታ ቀን፣ ነሐሴ ሃያ ስምንት የበረድ በዓላት በሚል የታወጀ ስለሆነ በዚያን እለት አረም የነቀለ፣ ለከብት የመነጠረ ለበረዶ ያጋልጣል፡፡ በእነዚህ ቀናት ስራ የሰራ በእድር ተጠይቆ ይወጣል አለዚያም በይቅርታ ይመለሳል" (ደን ግንቦት 01፣ 2017 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ በመሆኑም ከዚህ ማኅበራዊ እሴት በሚያፈነገጡ ግለሰቦች ምክንያት ለቡድኑ ችግር የሚያስከትሉ ተግባራትን ለመግታት ግስ የማንጻት ፋይዳ እንዳለው ይታመናል፡፡

የተጠኚው ማኅበረሰብ ዋናው ኢኮኖሚያዊ የመተዳደሪያ ሙያው የሰብል ምርት ከመሆኑ የተነሳ የበረድ አደጋ ለሰብል ምርታቸው ስጋት ይፈጥራል፡፡ የግስ ሥርዓት የበረድ አደጋ እንዳይከሰትና ከአደጋው ለመጠበቅ እንደሚረዳ ይታመናል፡፡ ‹‹...በክረምት ወቅት የተዘራው ሰብል በበረድ እንዳይመታ ለመጠበቅም ያግዛል›› (ደን፣ የካቲት 21፣ 2017 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ ስለሆነም፣ በግስ የደም ማፍሰስ ሥርዓት በመጠቀም በሚያመርቱት ምርት ላይ ለበረድ ተፈጥሯዊ አደጋ ከሚያጋልጥ አስከፊ መንፈስ ለመከላከል ስለሚረዳ ግስ ማኅበራዊነትን ከሚፈታተን ችግር ለማንጻት እንደሚረዳ ይታመንበታል፡፡

በግስ ሥርዓት ከሚነጹ የርኩሰት ክስተቶች በተጨማሪ ሰብልን የሚያወድም ደገዛ[15] ይጠቀሳል፡፡ ደገዛ ሰብሉ ለእሸት ሲቃረብ፤ ለፍሬ ሳይበቃ በአቋራጭ የሚያስቀርና በአንድ ሰው ሰብል ላይ ከተከሰተ

---

[13] አዋይ አድባሪት፡- ጠባቂ መንፈስ

[14] መስዋዕት፡- የሚቀርብ ስጦታ/መባ

[15] ደገዛ፡- አንበጣ

በሌላውም ሰብል የሚዛመት ነፍሳት ነው፡፡ በመሆኑም፣ ግስ በባሶሊበን ማኅበረሰብ ዘንድ ከንጽህናና ርኩሰት እሳቤ ጋር ተያይዞ ማኅበራዊ አብሮነትን ማስጠበቅና ከሰው ወደ ሰው፣ ከእንስሳት ወደ እንስሳት፤ ከሰብል ወደ ሰብል ከሚተላለፉ አጥፊ ነፍሳት ለመጠበቅ ይረዳል፡፡ "…ቸነፈር፣ በረድ፣ በሽታ ብቻ ሳይሆን እህላችን በደገዛ ሲበላም ከአንደኛው ሰብል ወደሌላኛው ስለሚዛመት ከዚህ ይጠብቀናል" (ልምጭም ቀበሌ፣ መጋቢት 23፣ 2017 ከተካሄደ ቃለመጠይቅ)፡፡ በመሆኑም፤ በሰብሎቻቸው ላይ ከባድ ጉዳት ከሚያደርሱ ክስተቶች ለመጠበቅ የሚረዳ እንደሆነ ከመረጃው መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ የተገለጹት የርኩሰት ክስተቶችን ለማንጻት በግስ ሥርዓት እርድ በመፈጸምና ደሙን ለእንስሳቱ በመርጨት፣ ሰዎቹ ከታረደው ስጋ በመብላት ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር በሥርዓቱ ለማስፈጸሚነት የተጠቀሙትን ምግብና መጠጥ በቦታው ተጠቅመው የመጨረስ ተግባሩን በመፈጸም ንጽሕናቸውን ያስጠብቃሉ፡፡ "ከዶሮ በስተቀር በደም መረጨት ሥርዓቱ ያልተካተቱ በረት ላይ የሚገኙ እንስሳት ለበሽታ ይጋለጣሉ የሚል ሥጋት አለ፤ ባለዛር ሆነው ሴተኛ አዳሪዎች ካሉ ከብቶቻቸውን ብር ከፍለውም ቢሆን ወደ ቅራቱ ይልካሉ" (ከአቶ ስመኝ ግንቦት 9፣ 2017 በቃለመጠይቅ)፡፡ በመሆኑም፣ በደም በመርጨት ሥርዓቱ ያልተካተቱ እንስሳት ላይ የጤና ችግር እንዳያስከትል በጥንቃቄ የመርጨት ተግባር ይፈጽማሉ፡፡ በሌላ መንገድ ደግሞ በግስ ሥርዓት የማንጻት ኃይል እንዳላቸው ከሚታመንባቸው ተግባራት አንዱ ምርቃት ነው፡፡ የክዋኔው ማብቂያ ሥርዓት ላይ የሚመርቀው በዕድሜ ከሌሎች ተሳታፊዎች የሚበልጠው ሰው ሲሆን፣ የተገኙትን ተሰብሳቢዎች ከአመሰገነ በኋላ ‹‹የፈሰሰው ደም፤ ለህጻን፣ ለአዋቂ፣ ለእንስሳት የሚበጅ ያድርግልን፤ ሀገራችንን ከበሽታ ከቸነፈር ይጠብቅልን፤ ሃገሩን አማን ገበያውን ጥጋብ ያድርግልን፤ የአንተ ነገር የአንቺ ነገር ከመባባል ያድነን በማለት ይመርቃሉ››፤ ታዳሚዎቹ ‹‹አሜን›› በማለት ይቀበላሉ፡፡ የምርቃት ቃላቱ የተሰዋው የበግ ደም ጠባቂ እንዲሆን ከቡድናዊ አደጋና ከግለሰቦች የጤና ማጣት እንዲጠብቃቸው የማድረግ ኃይል አላቸው፡፡ በጥቅሉ የቀረቡት የርኩሰት ክስተቶች ማኅበራዊ መስተጋብርን የሚያናጉ በመሆናቸው የግስ ሥርዓትን በመከወን በእንስሳት ደም መስዋዕት፣ በግሥ ሥርዓት በመሳተፍ፣ በምርቃት እንዲሁም ትርፍ ምግብና መጠጥ ወደ ቤት ባለመመለስ ከርኩሰት ክስተት ለመንጻት የሚያስችሉ ተግባራት መሆናቸውን መረጃዎች ያረጋግጣሉ፡፡

## ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት በትንተናው የቀረቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት በግስ ሥርዓት ማኅበራዊነትን ማስጠበቅ፣ ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ የንጽሕና ደንቦች/ መስፈርቶች፣ በግስ ሥርዓት የሚወገዱ የርኩሰት ክስተቶችንና የሚያነጹ ተግባራትን የሚያሳዩ መረጃዎች ተገልጸዋል፡፡ በግስ ሥርዓት የአተገባበር ሂደት ውስጥ የሚጠበቅ የማኅበራዊነት እሴትን በሚመለከት ለማኅበራዊ ችግር ስጋት ከሚሆኑ ተግባራት መቆጠብ፣ ታላቅን የማክበር፣ ቂምና ጥላቻን የማስወገድና እርቅና ይቅርታን በመተግበር ጥሩ ካልሆነ የምግባር ርኩሰት እንዲጠበቁ የሚያስችል ቡድናዊ ሥርዓት መሆኑን የመረጃ ትንተናው ያሳያል፡፡ እነዚህ ተግባራትን ለመፈጸም ሥርዓቱ በእድር በሚሳተፉ ሰዎች የሚፈጸም ሲሆን፣ የማስፈጸም ኃላፊነቱ ደግሞ በበረት አባት ይመራል፡፡ በሌላ መንገድ ደግሞ በግስ ሥርዓት ለመሳተፍ ከሚያስፈልጉ ደንቦች መካከል ከሰዎች ጋር የሚኖር ተግባቦት፣ መልካም ስነምግባርና በግስ ሥርዓቱ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማቅረብ፣ ለስለት የገቡትን ቃል መፈጸም የመታመን እሴትና ደንብን ያጠናክራል፡፡

በተጨማሪም በግስ ሥርዓቱ ለመሳተፍ የሚያሰባስበው የእድር አባልነት በቀድሞው ሥርዓት የሚከለከሉ የዘር ንጽሕናንና መጤነትን ለማሳተፍ የሚረዳ ሲሆን፣ የዛር መንፈስ የሌለባቸውና የሰዎች መልካም ስነምግባር በሥርዓቱ ለመሳተፍ እንደደንብ የሚታይ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ ሌላኛው በግስ ሥርዓት እንዲነጹ የሚፈለጉ ክስተቶች በቡድኑ ውስጥ የጋራ ጉዳት የሚያስከትሉ በመሆናቸው ከዚያ ለመጠበቅና ለመንጻት ደግሞ ለመስዋዕት የሚቀርበው የበግ ወይም የፍዬል ደም በዋናነት ይጠቀሳል፡፡ ለመንጻት እንሰሳቱን ከፈሰሰው ደም በመርጨትና ሰዎች በእርዱ በመሳተፍ፤ ከሚታረደው የበግ ሥጋ በመመገብ እንደሚጠበቁ ያምናሉ፡፡ የግስ ሥርዓቱ ማኅበራዊ ችግር ሲከሰት ብቻ የሚተገበር ሳይሆን በየዓመቱ የሚከወንና ከበራው ከተቋረጠ ለማኅበራዊ አብሮነት ስጋት የሚፈጥር የተፈጥሮ አደጋና ለሰውና እንሰሳት ሕይወት መቅሰፍት የሚያስከትል በሽታ በቀዬው ይከሰታል የሚል ስጋት ስለሚፈጠር ሳይቋረጥ ይከበራል፡፡

በጥቅሉ የጥናቱ ግኝት እንደሚያሳየው የግስ ሥርዓት የሚተገበረው ለማኅበራዊ ትስስር አደጋ የሚፈጥሩ ክስተቶችን ለማንጻት፣ የሰዎችንና የእንሰሳትን ጤና ለመፈወስና ሰብልን የሚጎዱ ነፍሳት እንዳይከሰቱ በግስ ሥርዓት ውስጥ በዋናነት በደም መፍሰስ የሚነጹበት ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ለመስዋዕት የሚቀርበው ደም የደህንነት ምሳሌ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሌላ መንገድ የሚከወኑት

*ሥርዓቶች የመንጻትና መርከስን ጽንስ ሐሳብ የሚያሳዩ ሲሆን፣ በግስ ሥርዓቱ የሚተገበሩ ደንቦችን መጠበቅ የንጽሕና መገለጫና ሥርዓቱን ባለማክበርና ደንቡን ባለመጠበቅ የሚከሰተው አደጋ ወይም ህመም ደግሞ ርኩሰት ስለመሆኑ የጥናቱ ግኝት ያረጋግጣል፡፡*

***የጥቅም ግጭት***

*ይህ ጥናት ከማንኛውም የጥቅም ግጭት ነጻ ነው፡፡*

***ምስጋና***

*የመስክ መረጃው ተሰብስቦ ለዚህ እንዲበቃ፣ እገዛ ላደረጋችሁልኝ ሁሉ አመሰግናለሁ፡፡ በተጨማሪም ግስ የሚከወንበትን ምክንያትና የሚጠናውን ማኅበረሰብ የሚመለከቱ መረጃዎችን አገኝ ዘንድ በወረዳው መስሪያ ቤቶች አብራችሁኝ ለተንከራተታችሁ ግለሰቦች፣ በመስክ መረጃ ስሰበስብ በሙሉ ፈቃደኝነት የጠየቋችሁን ሁሉ ከልባችሁ በመመለስ፣ ሥራዬ ቀላልና ምቹ እንዲሆን ሁኔታዎችን ላመቻቻችሁና በቃለመጠይቁ ለተሳተፋችሁ ሁሉ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡*

## ዋቢ ጽሑፎች

ሞላ ጀንበሬ፡፡ (2009) ፡፡ የነውር እሳቤ በሊቦከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እምነት [ያልታተመ ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተጠና]፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ http://etd.aau.edu.et/

ሰይድ መሀመድ፡፡ (2012) ፡፡ የወር አበባ የሕይወት ዑደት ሽግግር ሥርዓት በመንጌ ወረዳ በፋኩምኩም ጎሳ [ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተጠና ያልታተመ]፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ባሶ ሊበን ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ፅ/ቤት፡፡ (2009) ፡፡ ባህልና ኪነት(ያልታተመ)፡፡

አበበ ጥላሁን፡፡ (2013) ፡፡ የመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ አቀባበል ሥርዓት (ድግትስ ጋሕጃ) ትንተና በጉምዝ ብሔረሰብ ተተኳሪነት [ያልታተመ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተጠና]፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡

አያል ዋሴ፡፡ (2011) ፡፡ ነውር እንደ ልማዳዊ ህግ በደራ ወረዳ ማህበረሰብ [ያልታተመ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተጠና]፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ (2014) ፡፡ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ (1993) ፡፡ አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ይበልጣል አዳነ፡፡ (2015) ፡፡ የነውር እሳቤ ከወር አበባ እስከ ድኅረ ወሊድ በቤንች ብሔረሰብ [ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተጠና]፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ድርብ-ወርቅ፡፡ (2007)፡፡ የጉምዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓት በማንዱራ ወረዳ [ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተጠና]፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ https://etd.aau.edu.et/

ፀዳለ ታደሰ፡፡ (2007) ፡፡ በቀይት ንዑስ ወረዳ የሚከወኑ ሃገረሰባዊ እምነቶች [ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተጠና]፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ http://etd.aau.edu.et/

Abewa A. (2021). A History Of Baso-Libän *Wärӓda:* East Gojjam (1941-1991); partial fulfillment for MA thesis at Jimma university https://repository.ju.edu.et/

Antohin, A. E. (2014). Expressions of sacred promise: ritual and devotion in Ethiopian Orthodox praxis (Doctoral dissertation, UCL (University College London). https://discovery.ucl.ac.uk/

Akter, S. S. (2023). Akter, S. S. The Cultural Construction of Purity and Pollution under the Shades of Monipuri Social System in Bangladesh; Department of Anthropology
University of Rajshahi. https://www.researchgate.net/

Aspen, H. (1997). *Amhara traditions of knowledge: Spirit mediums and their clients*. Harrassowitz Verlag. https://www.abebooks.com/

Avichal. (2023*). Dignity of Life: Moral Philosophy, Organisational Theory, and Hostage Rescue-I.* https://dokumen.pub/

Bell, C. (2009). *Ritual: Perspectives and Dimensions.* Oxford University Press.https://voidnetwork.gr/

Brown, M. (2013). Emile Durkheim: Structural functionalism, adventure and the social order. In *Outdoor adventure and social theory* (pp. 23-33). Routledge.https://www.taylorfrancis.com/

Blidstein, M. (2017). *Purity, Community, and Ritual in Early Christian Literature*. Oxford University press.https://cris.haifa.ac.il/en/

Boudon, R. (2017). *The Origin of Values: Reprint Edition:Sociology and Philosophy of Beliefs*.Routledge. https://doi.org/10.4324/9781315133645

Cossu, T. (2024). The Pure and the Impure: Anthropological Approaches for the Study of the Ancient World. *Medea, 10*(1). https://ojs.unica.it/index.php/

Das, M. (2008). Menstruation as Pollution: Taboos in Simlitola, Assam. *Indian Anthropologist, 38*(2), 29–42. https://www.jstor.org/stable/41920072

Douglas, M. (1966). *Purity and danger: An analysis of concepts of pollution and taboo*. Routledge&KeganPaul.https://monoskop.org/

Douglas, M. (2003). *Purity and danger: An analysis of concepts of pollution and taboo*. Routledge. https://doi.org/10.4324/9780203361832

Duschinsky, R., Schnall, S., & Weiss, D. H. (2016). *Purity and danger now. New perspectives*; By Routledge. https://doi.org/10.4324/9781315529738

Fardon, R. (2016). *Purity and Danger. New perspective, Liberary of Congress*. https://www.routledge.com/

Feder, **Y.** (2016). Defilement, Disgust, and Disease: The Experiential Basis of Hittite and Akkadian Terms for Impurity*. Journal of the American Oriental Society, 136*(1), 99–116**.** https://doi.org/10.7817/jameroriesoci.136.1.99

Feder, **Y.** (2021). *Purity and pollution in the Hebrew Bible: from embodied experience to moral Metaphor*. Cambridge University Press. https://www.cambridge.org/9781316517574

Gray, K., Di Maggio, N., Schein, C., & Kachanoff, F. (2022). The problem of purity in moral Psychology. *Personality and Social Psychology Review, 27*(3), 272-308. https://doi.org/10.1177/10888683221124741

Headland, T. N., Kenneth, L. P., & Marvin, H. (Eds.). (1990). *Emics and Etics: The Insider/Outsider Debate*. Sage Publications.

Jordan, B. (2021). *Social Value in Public Policy*. University of Plymouth. DOI:10.1007/978-3-030-60421-9

Levine, D. N. (1965). *Wax and gold: Tradition and innovation in Ethiopian culture*. University of Chicago Press.https://press.uchicago.edu/l

Lockett, D**.** (2008). *Purity and Worldview in the Epistle of James.* T&T Clark.https://www.amazon.com/

Messing, S. D. (1957). The highland-plateau Amhara of Ethiopia. University of Pennsylvania. https://ehrafworldcultures.yale.edu/

McKinney, R.I. (2022). Purity. In: Mudimbe, V.Y., Kavwahirehi, K. (Eds) *Encyclopedia of African Religions and Philosophy*. Springer, Dordrecht. https://doi.org/10.1007/978-94-024-2068-5_322

Pankhurst, R. (1990). *A social history of Ethiopia. Institute of Ethiopian Studies*. https://doi.org/10.1017/S0021853700032473

Radcliffe-Brown, A. R. (1952). *Structure and function in primitive society*. Cohen & West. https://www.scirp.org/

Reimer, C. (2009). *the Taboo of Virginity: Purity Balls as Negative Rite of Passage at University of Toronto*. https://doi.org/10.26443/arc.v37i.516

Sato, T. (2011). Functionalism: It's axiomatic. University of Tokyo, *Sociopedia,* http://dx.doi.org/10.1177/205684601332

Turner, V. (1969). *The ritual process: Structure and anti-structure*. Aldine Publishing.https://monoskop.org/

Van Gennep, A. (1960). *The rites of passage*. University of Chicago Press. https://press.uchicago.edu/

Wandi, J. I., Afnita, N., & Hefni, H. (2021). Study of" Functional Structure" Emilie Durkheim Educational Anthropology on Character and Behavior Society. *Ikhtisar, 1*(1), 39-51. https://www.neliti.com/publications/351490/

Zesu, G. G. (2014). *The Sacred and the Profane-Environmental Anthropology of Ethiopian Orthodox Christianity*. Anchor Academic Publishing (aap_verlag). https://books.google.com.et/